# የኢፌዴሪ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
# FDRE ENVIRONMENTAL PROTECTION AUTHORITY

# በኢትዮጵያ የሊድ አሲድ ባትሪን በአግባቡ በመልሶ ዑደት ለመጠቀም የሚረዳ የቴክኒክ መመሪያ

2015 ዓ.ም

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Environmental Protection Authority

## መቅድም

ኢትዮጵያ በአፍሪካ በፍጥነት በማደግ ላይ ካሉ የኢኮኖሚ ባለቤቶች አንዷ ስትሆን 120 ሚሊዮን የሚገመት ሕዝብ አላት፡፡ የተሽከርካሪዎች በየጊዜው መጨመር፣ የእጅ ተንቀሳቃሽ ስልኮች መረብ መስፋፋት፣ የገጠሩ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ተደራሽነት መጨመር እና አስተማማኝ የሆነ የኃይል ማከማቻ ፍላጐት መጨመር ባትሪዎች በፍጥነት በሀገሪቱ ውስጥ እንዲሰራጩ አድርጓል፡፡ ምንም እንኳን ባትሪዎች ብዙ የልማት ግቦችን ለማሳካት ቢረዱም፣ አሁን ያለው የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ መዋቅር ጥቅም ላይ የዋሉ ባትሪዎችን ለመያዝ ስለማይችል አሳሳቢነታቸው ትልቅ ነው፡፡ አሳሳቢነቱ በተለይም በገጠራማው ማህበረሰብ ውስጥ የተሰራጩት ላይ ከፍ ያለ ነው፡፡ ባትሪዎች የፀኃይ ኃይልን በማጠራቀም የገጠሩን ማህበረሰብ የኤሌትሪክ ተደራሽ ለማድረግ ቢጠቅሙም እንኳን ከባትሪዎች ጋር ተያይዞ ያለውን አደገኛ ቆሻሻ በአግባቡ የሚይዝ መዋቅር ግን ገና አልተዘጋጀም፡፡ የሊድ አሲድ ባትሪዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት በጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል፡፡ በመሆኑም አግባብ ያልሆነ የሊድ አሲድ ባትሪ አያያዝና መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል ሂደት በሰው ጤናና በአካባቢ ላይ ከፋተኛ ጉዳት እንደሚያደርስ ይታወቃል፡፡ የተለያዩ የአፍሪካ አገራት ይህን የአደገኛ ቆሻሻ ብክለት ቅድሚያ እንዲሰጠው ትኩረት ያደረጉበት ሲሆን፣ የዓለምአቀፍ ማህበረሰቡም ይህን በመጋራት እ.ኤ.አ. በ2017 በተካሄደው 3ኛው የዓለም የአካባቢ ጥበቃ ስብሰባ ላይ ሁሉም ሀገራት "አካባቢ ጥበቃን ማዕከል ያደረገ ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪ አያያዛቸውን እንዲቀጥሉ" አበረታቷል (UNEA/EA.3/Res.9)፡፡

ይህ የቴክኒክ መመሪያ አካባቢ.ጥበቃን ማእከል ያደረገ አሰራር ያለው ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎችን በመልሶ ዑደት መጠቀም የሚያስችል አሰራርን የያዘ ነው፡፡

የቴክኒክ መመሪያው በኢትዮጵያ የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅን (አዋጅ ቁ.1090/2018) በመመስረት ለተረቀቀው አካባቢ ጥበቃን ማዕከል ያደረገ የሊድ አሲድ ባትሪ አያያዝ የህግ መመሪያ በቀጥታ አስፈላጊ የሆኑትን የቴክኒክ ዝርዝሮች ይዳስሳል፡፡

### ወሰን

ይህ የቴክኒክ መመሪያ ለሁሉም በኢትዮጵያ ውስጥ ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎችን በመልሶ ዑደት ሥራ ላይ ላሉ (ወይም ለመስራት በዕቅድ ላይ ላሉ) ሁሉ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ይዘቱም ቴክኒካዊ በመሆኑ በፋብሪካ ውስጥ ያሉ ሂደቶችንና የአስተዳደር እርምጃዎችን የያዘ ነው፡፡ ይህ መመሪያ በተራዘመ የአምራቾች ኃላፊነት ውስጥ የሚካተቱትን የፋብሪካ ምዝገባና የመዝገብ አያያዝ እርምጃዎችንና ሂደቶችን አልያዘም፡፡

በአጠቃላይ ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎች መልሶ ዑደት ሰሪዎች እራሳቸውን በሚከተለው ስዕላዊ መግለጫ በተገለጸው የሊድ አሲድ ባትሪ አያያዝ ሰንሰለት ውስጥ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡

ስዕል 1፡ በሊድ አሲድ ባትሪና ጥቅም ላይ በዋሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎች አያያዝ ውስጥ ያሉ የአሰራርና የቁሳቁስ ፍሰት አጠቃላይ እይታ



*የሊድ አሲድ ባትሪ ቸርቻሪዎች አንድ ወይም ከዚያ በላይ ማከፋፈያ ጣቢያዎች ሊኖሯቸው ይችላሉ:: ሁሉም ማከፋፈያ ጣቢያዎች ደግሞ ያገለገሉትን ለመሰብሰብ በመመዝገብ መተግበር አለባቸው:: መሰብሰቢያ ጣቢያዎች ደግሞ ከአከፋፋዮች ተለይተው ራሳቸውን መቻል አለባቸው::

⟶ የሊድ አሲድ ባትሪ ፍሰት

┈┈▶ ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎች ፍሰት

- - - - ▶ ለሊድ አሲድ ባትሪ መስሪያ የሚውሉ የጥሬ እቃዎች ፍሰት

ለሊድ አሲድ ባትሪ አምራቾች፣ ላገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪ የመሰብሰቢያ ጣቢያዎችና ለማጓጓዦች የሚውሉ ራሳቸውን የቻሉ መመሪያዎችም ተዘጋጅተዋል::

የሊድ አሲድ ባትሪዎችን ወደ አገር ውስጥ የማስገባት፣ መቸርቸርና ማከፋፈል ስራዎች ደህንነትን አደጋ ላይ የሚጥሉ ብክለቶች ጋር ተያያዥ ስላልሆኑ መመሪያ እንዳልተዘጋጀላቸው መገንዘብ አስፈላጊ ነው:: ሆኖም ግን አካባቢ ጥበቃን ማዕከል ያደረገ የሊድ አሲድ ባትሪ አያያዝ የህግ መመሪያው የባትሪ አከፋፋዮች ያገለገሉ ባትሪዎችን የመሰብሰቢያ ጣቢያዎች በመሆን እንዲያገለግሉ አስቀምጧል:: ስለሆነም የባትሪ ቸርቻሪዎችና አከፋፋዮች ተያያዥነት ያላቸውን ያገለገሉ ባትሪዎች የመሰብሰቢያ የቴክኒክ መመሪያዎች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለባቸው::

ከላይ የተገለፀው ስዕል 1 እራሱን የቻለ ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪ ማከማቻዎችን እንዳላስቀመጠም መገንዘብ አስፈላጊ ነው:: በተያያዥ የቴክኒክ መመሪያዎች ላይ እንደተገለፀው፣ ያገለገሉ ባትሪዎችን ማከማቻ ለመሰብሰቢያ ጣቢያዎችና ለመልሶ ዑደት መስሪያ ፋብሪካዎችም አስፈላጊ በመሆኑ ማከማቻ ለባትሪ አያያዝ ዑደት ራሱን የቻለና ብቻውን የሚቆም እንቅስቃሴ አይደለም:: ማከማቸት መታየት ያለበት ያገለገሉ ባትሪዎችን በመልሶ ዑደት ለማጓጓዝ ከማጠራቀም ጋር ወይም የተቀላጠፈ የመልሶ ዑደት ሂደትን ለመፍጠር ከማጠራቀም ጋር ከተያያዘ አግባብ ጋር ነው:: በመሆኑም ረቂቅ የህግ መመሪያው እራሱን የቻለ የባትሪና ያገለገሉ ባትሪዎች ማከማቻ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥን አልተመለከተም:: ምናልባት ከመልሶ ዑደት ስራ ጋር ግንኙነት የሌለው ትልቅ ማከማቻ ለመስራት የታቀደ ከሆነ ግን፣ እንደ ያገለገሉ ባትሪዎች መሰብሰቢያ ተመዝግቦ፣ በቴክኒክ መመሪያው መሰረት በደንቡ ላይ ለተቀመጡት መስፈርቶች መገዛት አለበት::

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Environmental Protection Authority

## ማውጫ


1.1 የፋብሪካው ያለበት ቦታ

1.2 የፋብሪካው አቀማመጥና ዲዛይን

2.1 የባለድርሻ አካላት መስተጋብር

3.1 ጤናና የኢንዱስትሪ ንጽህና

3.2 የሥራ ቦታ ደህንነት

4.1 ባትሪን መስበር

4.2 ሊድን ማውጣት

4.3 ሊድን ማቅለጥና መቅዳት

4.4 ማጣራትና ማጣመር

4.5 የተረፈ ምርቶች አያያዝ



The Federal Democratic Republic of ... Environmental Protection Authority

| # | ገጽታ | የተወሰኑ የቴክኒክ መመሪያዎች |
|---|---|---|
| **ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ሁኔታዎች** | | |
| 1.1 | ፋብሪካዉ ያለበት ቦታ | ያገለገሉ ሊድ አሲድ ባትሪዎች የመልሶ ዑደት ፋብሪካ ከመኖሪ ቤቶችና መኖሪያ አካባቢዎች፣ ከሆስፒታሎች፣ ከትምህርት ቤቶች፣ ከግብርና ቦታዎች፣ ከንግድ ቦታዎች፣ ከምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎችና ከሌሎች ከመኖሪያነት ጋር ግንኙነት ካላቸው ቦታዎች ርቆ መገንባት አለበት፡፡<br><br>ፋብሪካው ለማዕድን ማውጫ የዋለ ወይም የመሬት መንቀጥቀጥ ያለበት ያልተረጋጋ መሬት ላይ ወይም አደገኛ ቆሻሻ ወይም የከተማ ቆሻሻ መጣያ የነበረና ስጋት ያለበት መሬት ላይ መገንባት የለበትም፡፡ ፋብሪካው በላይኛው የወንዝ ተፋሰስ ወይም በከርሰ ምድር ውኃ ጉድጓድ ወይም የመጠጥ ውኃ ምንጭ አካባቢ መመስረት የለበትም፡፡ የፋብሪካው አካባቢና የሚያከናውነው ስራ ስሱ የሆኑ የእፅዋት ወይም የእንስሳት ዝርያዎችን፣ የወፎችን ማረፊያዎች፣ የድንበር ተሻጋሪ ወፎችን መሸጋገሪያ መንገድና ስነምህዳሩን የሚረብሽ መሆን የለበትም፡፡ የፋብሪካው ቦታ እንደ ጐርፍ፣ የመሬት መንሸራተት ወይም ናዳ ካሉ የተፈጥሮ አደጋዎች የተጠበቀና ብክለትን ወደ አካባቢው ከመልቀቅ የተቆጠበ መሆን አለበት፡፡<br><br>ከፍ ያለ የአካባቢ ብክለት መጠንን ማስከተል የማምረቻ ፋብሪካውን የጤናና የአካባቢ ደህንነት እንዲሁም የስራ ፈቃድ እስከማስነጠቅ ያደርሳል፡፡ ፋብሪካው በተወሰኑ የአየር ንብረቶች ወቅት ለሚከሰቱ የልቀት ክምችትን ይዘው ማቆየት በሚችሉ ሸለቋማ ቦታዎች መመስረት የለበትም፡፡<br>ያገለገሉ ሊድ አሲድ ባትሪ የመልሶ ዑደት ፋብሪካዎች በተከለሉ የኢንዱስትሪ ቦታዎች ወይም የአፈር ይዘት የማስተካከያ ሕክምና የተደረገላቸውና የተለቀቁ የኢንዱስትሪ ቦታዎች ላይ ቢገነቡ ጥሩ ነው፡፡ ብክለትን፣ የማስተካከያ ሕክምናንና የተረጋጋ መሬት ማግኘትን በተመለከተ ቦታውን በትክክል የመዳሰስ ስራ መሰራት አለበት፡፡ አሁን ስራ ላይ ያሉ አዳዲስ ባትሪዎችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች ያሉበት ቦታ፤ ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎችን የመልሶ ዑደት ስራ ላይ በማዋል የተሰማሩ ፋብሪካዎችን ባቅራቢያ ለመገንባት ምቹ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡<br>ያገለገሉ ባትሪዎችን የሚያቀርቡ ከባድ መኪኖች አደጋ እንዳይደርስባቸው የመንገዱ አሰራር ጥሩና ምቹ መሆን አለበት፡፡ መንገዶች ብዙ የጫኑ ከባድ መኪኖችን በጭቃ ከመያዝና በመሬት መንሸራተት ከመጠቃት የሚከላከሉ መሆን አለባቸው፡፡ የመኖሪያ ቤቶችና የግብርና ስራዎች ወደ ፋብሪካው ተጠግተው እንዳይመሰረቱ የፋብሪካው አስተዳደር ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ጥብቅ ግንኙነት የማድረግ ኃላፊነትን መውሰድ አለበት፡፡<br>ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የተመሰረቱና ከላይ የተጠቀሱትን አንዱን ወይም ከአንድ በላይ መስፈርቶችን የማያሟሉ ከሆነ አካባቢውንና ነዋሪውን እንዲሁም ሰራተኞችን ከብክለት ለመጠበቅ ሲባል እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው፡፡ አደጋዎቹ ሊወገዱ የማይችሉ ከሆነ ፋብሪካው ወደ ሌላ ቦታ ሊዘዋወርና ቦታው የማስተካከያ እርምጃ እንዲያገኝ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ |
| 1.2 | የፋብሪካው አቀማመጥና ንድፍ | ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎችን መልሶ ውደት የሚሰራው ፋብሪካ ባትሪን ከመስበር እስከ ሊድን ማቅለጥ፤ እንዲሁም የፕላስቲክ ማቀፊያዎችን በመልሶ ዑደት መስራት፣ የሊድ አሲድን፣የጋስ ልቀትን፣የሊድ ብናኝን፣ ዝቃጭንና የሊድ ቅሬቶችን አያያዝ በተቀናጀ መልኩ መስራት በጣም አፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም በምርት መካከል የሚገኙትን ቅሬቶችና ተረፈ ምርቶችን መያዝና ማጓጓዝ ሁልጊዜም ፍሳሽ ስለሚኖረው ለከፋ የሰው ጤናና የአካባቢ አደጋ መንስኤ ይሆናል፡፡ ማንኛውም የባትሪ ሰበራም ይሁን የአሲድ ማፍሰስ ስራ ከተቀናጀው ስርዓት ውጭ መከናወን የለበትም፡፡ ለውጤታማና ደህንነትን ለጠበቀ የሊድ መልሶ ዑደትና ለጥሩ የተረፈ ምርቶች አያያዝ፤ ውጤታማ የሆነ ተሸከርካሪ ወይም ሌላ ዘመናዊ ማቀለጫን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡<br>በፋብሪካው ውስጥ ሊኖር የሚገባውን መሠረታዊ የስራ ደህንነት በተመለከተ፤ ሁሉም ቢሮዎችና ያገለገሉ ባትሪዎች የመልሶ ዑደት ፋብሪካ የስራ ክፍሎች የእሳት አደጋ ማስጠንቀቂያዎች ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በሰው የሚዘወሩ የእሳት አደጋና የድንገተኛ አደጋ ማስጠንቀቂያ ቁልፎች በሁሉም ያገለገሉ ባትሪዎች የመልሶ ዑደት ፋብሪካ የስራ ክፍሎች ውስጥ መኖር አለባቸው፡፡ ድንገተኛ አደጋ በሚያጋጥምበት ወቅት ጥቅም ላይ ይውሉ ዘንድ የአደጋ ጊዜ መውጫዎች በትክክል ተፅፈው የመውጫ ምልክቶች ብርሃን እንዲኖራቸው ይገባል፡፡ ፋብሪካው ለእያንዳንዱ የማምረት ሂደት ክፍል የተለያዩ የእሳት ማጥፊያዎችን መጠም አለበት፡፡ የእሳት ማጥፊያዎች በቀላሉ እንዲደርሱና እንዲያዙ ከመሬት በላይ በ75 ሳ.ሜ ከፍታ መቀመጥ አለባቸው፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| | | በክፍል 4 እና 5 ከተቀመጡት የቴክኒክ መስፈርቶች ባሻገር፣ ፋብሪካው የልብስ ማጠቢያ ማሽን፣ የልብስ መለወጫ ክፍሎች እና የመታጠቢያ ቦታዎች ሻወርን ጨምሮ ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህም የሊድ ብናኝ ከፋብሪካው ወደ ንጽህ ቦታዎችና ወደ ውጭም እንዳይወጣ ይከላከላል፡፡ ለሴቶችና ለወንዶች ልብሳቸውን የሚቀይሩበትና ገላቸውን የሚታጠቡበት የተለያዩ ክፍሎች ሊኖሯቸው ይገባል፡፡ ኩሽና እና የመመገቢያ ቦታ ካለ ደግሞ ሠራተኞች የተበከለ ልብስ ለብሰው እንዳይገቡ ንፁህ ልብስ በሚቀይሩበት ክፍል በኩል መግቢያ ሊኖረው ይገባል፡፡ በተጨማሪም የድንገተኛ የዓይን አደጋ መታጠቢያ ቦታዎችና ወይም የድንገተኛ አደጋ መከላከያ የገላ መታጠቢያ ቦታዎች ሠራተኞች ከባትሪ አሲድና ወይም ከፍተኛ የሊድ ብናኝ ጋር በሚጋለጡበት ቦታዎች አቅራቢያ መኖር አለባቸው፡፡<br><br>ሁሉም የሊድ መልሶ ዑደት ፋብሪካ ክፍሎች ምቹና ለስላሳ፣ ለማዳለጥ የማያጋልጡ፣ ውኃ የማያሰርጉ፣ በቀላሉ የሚታጠቡና እንደ የአሲድ መደፋትን ዓይነት ብክለትን በቶሎ ማጽዳት የሚያስችሉ ወለሎች ሊኖሯቸው ይገባል፡፡ ወለሉ የነቃና ክፍተት ኖሮት አቧራና ሌሎች ንጥረ ነገሮችን እንዳያከማች ሆኖ መሰራት አለበት፡፡ የባትሪ ሰበራ በሚካሄድበት ክፍል ደግሞ ወለሉ አሲድን የሚቋቋም ሆኖ መሰራት አለበት፡፡ ማንኛውም ለንጽህና የሚውል ፍሳሽ ሳይታከም ከፋብሪካው እንዳይወጣ ፍሳሽን የሚይዝ፣ ፍሳሽን የሚያስወግድና የሚያክም ስርዓት አብሮ መገንባት አለበት፡፡<br>የተበከለ አየር ከፋብሪካው እንዳይወጣ ለማድረግ ሁልጊዜም ንፁህ አየር ከውጭ በቀጥታ እንዲገባ በማድረግና የሚወጣውን አየር በማጣራት እንዲሁም ብናኙን ስብስቦ በመልሶ ዑደቱ ማቃጠያ ውስጥ በማስገባት የምርት ወደ መልሶ ዑደት ማስገባት ይቻላል፡፡ |
| 2.1 | የባለድርሻ አካላት መስተጋብር | በፋብሪካው ተፅዕኖ የሚደርስባቸው ሰዎች ሁሉ ስለመልሶ ዑደቱ ሂደት ስለሚያስከትለው የጤናና የአካባቢ ደህንነት አደጋ እና አደጋን ለመቀነስ ስለሚወሰዱት እርምጃዎች መረጃ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የእነርሱም ስጋቶች ሊደመጡና ጥያቄዎቻቸውም ሊመለሱላቸው ይገባል፡፡ ንግግሮቹም ግልጽና ስጋቶች የሚያቀርቡበትም መንገድ ስም አልባ መሆን ይገባዋል፡፡ ምቹ የሆኑ የሐሳብ ልውውጦችም ግልጽ የሆነ የጋራ ስብሰባን ከማካሄድ እስከ አንድ ለአንድ እና ስም አልባ የሆነ ቀጥተኛ የብየነ መረብ ግንኙነት ወይም በእንባ ጠባቂ በኩል የሚደረግን ውይይት ያካትታል፡፡ የቀረቡ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ማግኘት አለባቸው፡፡ የተሟላ የጥያቄዎችና የመልሶቹ ሰነድም ጥያቄ በቀረበ ጊዜ ለመርማራዎች እና ለአካባቢው ወይም ለፌዴራል ባለስልጣናት ይሰጣል፡፡ ባገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪ የመልሶ ዑደት ፋብሪካው አካባቢ ለሚኖሩ ሰዎችና ለሠራተኞች በየጊዜው በደም ውስጥ ያለ የሊድ መጠን ምርመራ መካሄድ አለበት (3.1ን ይመልከቱ)፡፡ በተጨማሪም ከሁብረተሰቡ በሚቀርብ ጥያቄ መልስ ሊሰጥ በሚችል መልኩ የገፀ ምድር ውኃና የአፈር ምርመራ በየጊዜው መደረግ አለበት፡፡ የውኃ እና የአፈር ናሙና አወሳሰድና የምርመራው ውጤት ተዓማኒነትና ግልጽነት ዋስትና እንዲኖረው፣ እራሱን ችሎ በቆመ ሶስተኛ ወገን ሳይንሳዊ ዘዴ መከናወን አለበት፡፡ ውጤታማ የሆነ የባለድርሻ አካላት መስተጋብር ከሚይዛቸው ጠቃሚ ነጥቦች ውስጥ (1) አሳሳቢ ጉዳዩችን ማዳመጥ (2) ሐቀኛ ምላሽን መስጠት (3) የአካባቢውን ማህበረሰብ ጤናና ደህንነት ለመጠበቅና ችግሮችን ለመፍታት ቁርጠኝነትን ማሳየት ናቸው፡፡ |
| 3.1 | ጤናና የኢንዱስትሪ ንፅህና | ***በየጊዜው የሚደረግ የጤና ምርመራ፡*** በሊድ አሲድ ባትሪ ማምረቻ ውስጥ የሚሰሩ ጊዜያዊም ይሁን ቋሚ ሁሉም ሠራተኞች ከክፍያ ነፃ የሆነ በፋብሪካው ውስጥ የሚከናወን በየስድስት ወሩና በየአስራ ሁለት ወሩ የጤና ምርመራ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ የጤና ምርመራውም በተመዘገቡ የጤና ባለሙያዎች ማለትም በዶክተሮች እና/ወይም በነርሶች መካሄድ አለበት፡፡ አጠቃላይ የጤና ምርመራው ከደም ምርመራ ጋር አብሮ ሊካሄድ ይችላል፣ አንዱ ሌላውን ግን አይተካም፡፡ አዲስ ሠራተኛ በሚቀጠርበት ጊዜ የጤና ምርመራ በማካሄድ የጤንነት ውጤቱን መዝገብ ማስረከብ እንደ አግባብ ይወሰዳል፡፡ ይህ የመጀመሪያ ዳሰሳ ከስራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን በሽታዎች ከነባር በሽታዎች ለመለየት እንደ መነሻ ያገለግላል፡፡<br><br>ከሥራ ጋር ግንኙነት ላላቸው የጤና እክሎች የሕክምና ድጋፍ፣ ምክር፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ ሙሉ ሕክምናን መስጠት ያስፈልጋል፡፡ የጤና ስጋቶችና መንስኤዎቻቸው በትክክል መለየትና በተቻለ መጠንም ጫናቸው መቃለል አለበት፡፡ |

*በደም ውስጥ ያለን የሊድ መጠን መመርመር፡* በደም ውስጥ የሚገኝ የሊድ መጠን ተዓማኒ የሆነ ከስራ ጋር ግንኙነት ያለው የሊድ ተጋላጭነትን ስለሚያሳይ ሁሉም በሊድ አሲድ ባትሪ የመልሶ ዑደት ፋብሪካ ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች መደበኛ የደም ምርመራ ማካሄድ አለባቸው:: የደም ምርመራውም በጤና ባለሙያዎች መካሄድና ናሙናዎችም እውቅና በተሰጣቸው ቤተሙከራዎች መከናወን አለባቸው:: ይህ አቅም በሌለበት ሁኔታ ግን በባለሙያ የተደገፈና ተዓማኒ የሆነ ተንቀሳቃሽ የመስክ መመርመሪያ መጠቀም ያስፈልጋል::

የአካባቢ ጥበቃን ማዕከል ያደረገ የሊድ አሲድ ባትሪ አያያዝ የህግ መመሪያ ላይ በተቀመጠው መሠረት በደም ውስጥ ሊገኝ የሚገባውን ከፍተኛው መጠን እንደወሰን ሊወሰድ ይገባዋል:: በባዝል ስምምነት በተመሠረተው የቴክኒክ መመሪያ መሠረት ከ30 ማይክሮ ግራም በዴሲ ሊትር በታች የሆነ በደም ውስጥ ያለ የሊድ መጠን የሰው ጤናን ለመጠበቅ አስፈላጊ ወሰን ሲሆን፤ ከ20-30 ማይክሮግራም በዴሲ ሊትር የሆነ የሊድ መጠን በደም ውስጥ ሲገኝ ተቀባይነት ያለው የአደጋ መጠን ተብሎ ተተርጉሟል:: የሊድ ተጋላጭነትን ለመቀነስ ይረዳ ዘንድ የማስጠንቀቂያ መጠኖችን ለመለየት የስራ ክፍሎችንና የተጋላጭነት መንገዶችን ማሰስ ያስፈልጋል:: ከማስጠንቀቂያ መጠኖች በተጨማሪ የተጐዱ ሠራተኞች በደማቸው ውስጥ ያለው የሊድ መጠን እስኪቀንስ ድረስ ጉልህ በሆነ መልኩ ዝቅተኛ ተጋላጭነት ወዳላቸው የሥራ ክፍሎች መዛወር አለባቸው::

ከፍ ያለ የሊድ መጠን በደም ውስጥ ሲገኝ የጤናና የአካባቢ ደህንነት ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ጉድለት የሚያሳይ ሲሆን ለሠራተኞችና ለጐብኝዎች የተሻለ የጥበቃ ዋስትናን ለመስጠት የደህንነትና የንጽሕና እርምጃዎች ላይ ሰፋ ያለ ግምገማ ማካሄድ ያስፈልጋል:: የተለያየ የስራ ቦታዎች የተለያየ የአደጋ ደረጃዎች ጋር ይያያዛሉ:: በባትሪ ሰበራ፣ ሊድን በማቅለጥ፣ በማጣራት፣ በጭስ ማውጫ የጋዝ ሕክምና እና በጥገና ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች ከፍተኛ የአደጋ ተጋላጭ በመሆናቸው ቢያንስ በየሶስት ወሩ ሊመረመሩ ይገባል:: በደም ውስጥ ሊኖር የሚገባው የሊድ መጠን ወሰኑ ካለፈ፤ ከአንድ ወር በኋላ የክትትል ምርመራ መካሄድ አለበት:: በባትሪ መልሶ ዑደት ፋብሪካ ውስጥ የሚሰሩ ሌሎች ሠራተኞች ሁሉም መካከለኛ የአደጋ ተጋላጭ ተብለው የሚመደቡ ሲሆን በየስድስት ወሩ መመርመር አለባቸው:: የማስጠንቀቂያ ወሰኑን አልፎ ከተገኘ፤ የክትትል ምርመራው ከሶስት ወር በኋላ መደረግ አለበት:: የቢሮ ሥራ የሚሰሩ፣ ምግብ ቤትና የልብስ ንጽሕና መስጫ ላይ የሚሰሩ ሠራተኞች ዝቅተኛ የአደጋ ተጋላጭ ተብለው የሚመደቡ ሲሆን ቢያንስ በየ12 ወሩ መመርመር ሲኖርባቸው፤ የክትትል ምርመራውም ከ6 ወር በኋላ መካሄድ አለበት:: የተገለፁት መጠኖች በጐልማሶች ላይ ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው:: ልጅ በመውለድ እድሜ ላይ የሚገኙ ሴቶች አጠቃላይ ማህበረሰቡ ሊኖረው ከሚችለው የሊድ መጠን በላይ ሊኖራቸው አይገባም:: በማንኛውም የሊድ አሲድ ባትሪ መልሶ ዑደት ፋብሪካ አካባቢ ሕፃናት ሊኖሩ አይገባም::

በደም ውስጥ ያለ የሊድ መጠን የምርመራ ውጤት በትክክል ተመዝግቦ ለተመረመረው ሰው፣ ለኢንዱስትሪው ዶክተር ወይም ነርስ እና ለኢንዱስትሪው የስራ አመራር ሊሰጥ ይገባዋል:: በትክክል ተመዝግቦ የተደራጀው ውጤት ተቆጣጣሪ ኦዲተር በሚጠይቅበት ጊዜ ሊሰጥ ይገባል::

የሊድ አሲድ ባትሪ የመልሶ ዑደት ፋብሪካው በሰዎች መኖሪያ አካባቢ ያለ ከሆነ፣ ፋብሪካው ለነዋሪዎቹ የሊድ ብክለት ምርመራ ሊያደርግላቸው ይገባል::

ምንነቱን መለየት አስቸጋሪ ከሆነ ከስራ ተጋላጭነት ጋር የተገናኘ የጤና እክል የተገኘ እንደሆነ፤ የጤና ክፍሉ ይህንን ለፋብሪካው አመራር ማሳወቅ ሲኖርበት የበሽተኛውን ክብርና ግላዊ መረጃ ግን መጠበቅ አለበት:: በደም ውስጥ ከፍ ያለ የሊድ ልኬት መገኘት ለሠራተኛ መባረር ምክንያት መሆን የለበትም:: ነገር ግን ለሠራተኛው የተሻለ የተጋላጭነት መከላከያን ለመስጠት፣ ለማማከር፣ ጠቃሚ መመሪያና አስፈላጊ ከሆነ ድጋሚ ስልጠና ለመስጠት ምክንያት ሊሆን ነው የሚገባው::

ሠራተኞችንና ጐብኝዎችን ከብክለት መከላከል ይቻል ዘንድ፣ ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎች ላይ ስራ በሚሰራበት ጊዜ ሁሉ እያንዳንዱ ሰው የግል መከላከያ ትጥቆችን መጠቀም አለበት:: የግል መከላከያ ትጥቆች ከሊድ ብናኝ፣ ከአሲድ፣ ከሙቀት፣ ከሚወድቁ ዕቃዎች፣ ጆሮን ከሚጐዳ ጩኸትና አካልን ከሚጐዳ አደጋ ይከላከላሉ:: ስለሆነም የግል መከላከያ ትጥቆች ለሁሉም ሠራተኛ በበቂ ቁጥርና በተፈላጊው ጥራት በነፃ ሊሰጡ ይገባል:: ሠራተኞችም የየራሳቸው የግል መከላከያ ትጥቅ ሊኖራቸውና የእራሳቸውን ትጥቅ ብቻ ሊለብሱ ይገባል:: የግል መከላከያ ትጥቆች በየጊዜው ሊፀዱና

ሊጠገኑ ይገባል፡፡ አስፈላጊ ከሆነም ሊተኩ ይገባል፡፡ ልብስነት ያላቸው የግል መከላከያ ትጥቆች ከስራ በኋላ ሁሌም ሊታጠቡ ይገባል፡፡ ለመተንፈሻ መከላከያ የሚመከረው ሐምራዊ ቀለም ያለውና ከፍተኛ ብቃት ያለው ልዩ የአየር ቅንጣት ማስወገጃ የተገጠመለት ኔፕሮን መተንፈሻ ነው፡፡ ለአንድ ጊዜ ጥቅም ብቻ የሚውሉት ጭምብሎች እነንደ ኤን 95 (N 95) እና ኤፍ ኤፍ ፒ 2 (FFP2) ያሉት ከእያንዳንዱ ሽፍት በፊት ወይም ከበዛ ከ8 ሰዓታት ጥቅም በኋላ ሊተኩ ይገባል፡፡ ባትሪዎችን በመስበር ስራ ላይ ለተሰማሩ ሠራተኞች የሚሰጧቸው ጭንብሎች የአሲድ ጭጋግን ማስወገድ የሚችሉና ካርቦንን ማጣራት የሚችል ማጣሪያ የተገጠመላቸው መሆን አለባቸው፡፡ የብናኝ ማለፊያና ማከማቻን ለመጠገን፣ አተነፋፈስን በራሱ የሚያግዝ መተንፈሻን መጠቀም አለብን፡፡ ለመተንፈሻ መሳሪያዎች ውጤታማነት መሠረታዊው ጉዳይ በትክክል ፊት ላይ መግጠም መቻላቸው ነው፡፡

አስፈላጊ የሆኑ የግል መከላከያ ትጥቆችን ጨምሮ ሌሎችንም መረጃዎች በተለያዩ የፋብሪካው ክፍሎች በማሽኖችና በመሳሪያዎች ላይ በግልጽ በሚታይበት ሁኔታና ቀለል ባለ ምልክት ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው፡፡

*ንፁህ ቦታዎች፡* የመልሶ ዑደት ፋብሪካው የሊድ ብናኝ ከፋብሪካው ወደ ንፁህ ቦታዎችና ከፋብሪካውም ውጭ እንዳይወጣ ለማድረግ፣ ለሠራተኞች የልብስ መቀየሪያ ክፍሎችንና የገላ መታጠቢያ ክፍሎችን ማሟላት አለበት (አባክዎን 1.3ን ይመልከቱ)፡
፡

የሊድ ብናኝ ሠራተኛው ሲሰራ በተጠቀመው ልብስ፣ በእጅና በፀጉር አማካኝነት ሊወጣ ይችላል፡፡ በፋብሪካው ያለ የልብስ ንፅሕና መስጫ ሠራተኞች ስራ በሚጀመሩበት ቀን ወይም ፈረቃ ጊዜ ንፁህ የስራ ልብስ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ እንዲሁም ጥራትና ብቃት ያላቸው ሳሙናዎችና ፎጣዎች ለሠራተኞች ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
ንፁህ ልብሶችና የተበከሉ የስራ ልብሶች መቀላቀል የለባቸውም፡፡ መመገቢያ አዳራሹና ኩሽናው ንፁሕ መሆን ያለባቸው ክፍሎች በመሆናቸው ንፁህ ልብስ ብቻ ተለብሶ ሊገባባቸው ይገባል እንጂ በተበከለ የስራ ልብስ ሊገባባቸው አይገባም፡፡ ወደ ምግብ አዳራሽ ከመግባት በፊት እጅ እስከ ክንድ ድረስና ፊቶች መታጠብ አለባቸው፡፡

በተጨማሪም ሠራተኞች ለባትሪ አሲድና የሊድ ብናኝ በጣም ተጋላጭ በሆኑባቸው ቦታዎች ሁሉ የአደጋ ጊዜ የዓይን መታጠቢያ እና/ወይም የገላ መታጠቢያ መኖር አለበት፡፡

*የመልሶ ዑደት ፋብሪካውን ስለማጽዳት፡* ፋብሪካው ብናኝን በማያጠራቅም መልኩ ቋሚ በሆነ እርጥብ የአፀዳድ ዘዴና ብናኞችን በአግባቡ በሚይዝ መልኩ መፀዳት አለበት፡፡ በባለሙያ የታገዘ ከፍተኛ ብቃት ያለው ልዩ የአየር ቅንጣት ማስወገጃ የተገጠመለት ደረቅና እርጥብ የቫኪዩም ማፅጃና መፈቅፈቂያ ያስፈልጋል፡፡ የተፀዳበት ውኃም ከፋብሪካው የሚወጣ ፍሳሽ በሚታከምበት መንገድ መታከም አለበት፡፡ ሠራተኞችና ማፅጃ መሳሪያዎች ከውኃ ጋር የተቀላቀለ ሰልፈሪክ አሲድና የባትሪ ፈሳሽ ፍሳሽ እንደሚያጋጥማቸው በማሰብ በፅዳት ክፍለ ጊዜዎች ሌሎች ሠራተኞችና ጐብኝዎች እንዳይጋለጡ መደረግ አለበት፡፡ ሁሉም የመልሶ ዑደት ፋብሪካው ክፍሎች ንፅህና የተጠበቀ መሆን አለበት፡፡ የፋብሪካውን ስራ ለማቀላጠፍና የፅዳት ስራውንም እንዳያደናቅፍ፤ በመረማመጃ የስራ ቦታዎች ሁሉ አላስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች እንቅፋት እንዳይፈጥሩ መንገድ መዝጋት የለባቸውም፡፡ ብናኞች በቀላሉ እንዲረጉና እንዳይበኑ ለማድረግ፣ ወለሎች እርጥበት እንዲኖራቸው ይመከራል፡፡ አቧራ እንዳይበንና ሠራተኞች ለብናኝ ተጋላጭ እንዳይሆኑ በደረቁ መጠረግ የለባቸውም፡፡

*ለደህንነት የሚጠቅሙ የሰዎች ጥንቃቄ* እያንዳንዱ የሊድ አሲድ ባትሪ የመልሶ ዑደት ፋብሪካ ሠራተኛና ጐብኝ የራሱንና የስራ ባልደረቦቹን ጤንነትና ደህንነት መጠበቅ የሚያስችል ባህሪ እንዲኖረው ይገባል፡፡ መሠረታዊ መመሪያዎቹም፣

- የሊድ ብናኝ በባዶ ሆድ በቀላሉ ስለሚዋሃድ፣ አንድ ሰራተኛ ስራ ከመጀመሩ ቢያንስ ከአንድ ሰዓት በፊት ምግብ መመገብ አለበት፡፡
- ዋናው ከስራ ጋር ተያያዥነት ያለው የሊድ ተጋላጭነት እንደመመገብና ማጨስ ባሉ ተግባራት ሊድን ከእጅ ወደ አፍ በመዋጥና በመማግ የሚከሰት

| | | |
|---|---|---|
| | | መሆኑን መገንዘብ<br>• ተገቢ የሆኑ የሥራ አልባሳት መልበስ<br>• ተገቢ የሆኑ የግል መከላከያ ትጥቆችን በትክክለኛው መንገድ መልበስ<br>• የሥራ ቦታዎችን ንፁህ፣ የፀዱና ከሊድ ብናኝ የነፁ ማድረግ<br>• አቧራና ብናኝን በደረቅ መጥረጊያ ሳይሆን በእርጥብ መወልወያ ማጽዳት<br>• ደህንነትን የሚጠብቁ የሥራ ልምምዶችን ማክበር፣ ለምሳሌ መሰላሎች እንዳይወድቁ አድርጎ ማሰር፣ ከፍ ያለ ቦታ ላይ ሲሆን በትክክለኛው መርገጫ ላይ ሆኖ መስራትና የተጨናነቁ የስራ ቦታዎች ውስጥ ሲገባ ከስራ ቦታው ተቆጣጣሪ ጋር መግባትን ያካትታል፡፡<br>• የሰውነትን የውኃ ይዘት ለመጠበቅ በበቂ ሁኔታ ውኃ መጠጣት<br>• በሐኪም የታዘዘ መድኃኒት መውሰድ ካልሆነ በስተቀር፣ በስራ ቦታ በምንም ዓይነት አለመብላት፣ አለመጠጣትና አለማጨስ<br>• በእያንዳንዱ የስራ ክፍለ ጊዜ፣ ወይም የቀኑ ስራ በሚያበቃበት ጊዜ ገላን በሳሙና መታጠብ<br>• የሊድ ብናኝ ወደ ንፁህ ቦታዎች ወይም ከስራ ቦታ ውጭ እንዳይወጣ ለማድረግ እያንዳንዱ ሠራተኛ የስራ ክፍለ ጊዜውን ሲጨርስ የቆዳውንና የጥፍሩን ንጽሕና ማረጋገጥ<br>• በፋብሪካው ውስጥ ብክለት ሊኖርበት የሚችል አካባቢ ሲሰራበት የነበረን ልብስ እንደለበሱ ከፋብሪካው አለመውጣት<br>• የሥራ ልብሶችን፣ የስራ ጫማዎችንና የግል መከላከያ ትጥቆችን በስራ ቦታ መተው እንጂ ወደ ቤት አለመውሰድ<br>• መደበኛ የሆኑ የሕክምና ቀጠሮዎች ላይ መገኘት |
| 3.2 | የሥራ ቦታ ደህንነት | እያንዳንዱ የሊድ አሲድ ባትሪ የመልሶ ውደት ፋብሪካ ሠራተኞቹ ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ ቦታን ለመፍጠርና ለማስቀጠል ቁርጠኛ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የደህንነት ፖሊሲ ሊኖረው ይገባል፡፡ ፈቃዳቸውን የሚያረጋግጥ መግለጫ መያዝ ብቻ ሳይሆን ፓሊሲውን እንዴት እንደሚፈጸምም ዝርዝር መግለጫ ሊያቀርብ ይገባዋል፡፡ የደህንነት ፖሊሲው ውጤታማ ሆኖ ይተገበር ዘንድ የተግባቦት ግንኙነት፣ ስልጠናና እሰሳ አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ ፓሊሲው ሊይዛቸው የሚገባውም፡-<br>1. የፈቃደኝነት መግለጫ<br>2. የሠራተኛውን ስምና አድራሻ የያዘ የኃላፊነት ዝርዝር እና<br>3. የፓሊሲውን አተገባበር የያዘ ዝርዝር ማብራሪያ ናቸው፡፡<br>የመጨረሻው ነጥብ የሚከተሉትን ያካትታል፡፡<br>• በተለያየ የሊድ አሲድ ባትሪ የመልሶ ውደት ፋብሪካ ክፍሎች ፖሊሲው በምን መልኩ መተላለፍና መታየት እንዳለበት የሚያመለክት መግለጫ<br>• ለእያንዳንዱ የስራ መስክ የሚያስፈልጉ የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች ዝርዝር<br>• የደህንነት ምልክቶች እንዴት መለጠፍ እንዳለባቸው የሚያዝ ውሳኔ<br>• ለእያንዳንዱ የሊድ አሲድ ባትሪ ማምረቻ ሰንሰለት የሊድ ተጋላጭነት ዳሰሳን ለማካሄድ የሚረዳ ተጨባጭ ዕቅድ<br>• ለጥገናና በጥገና ጊዜ መዝጋትን የሚያመለክት መመሪያ<br>• የእሳት አደጋና ፍንዳታን ለመከላከል የሚረዱ ዝርዝር እርምጃዎች<br>• ለአዳዲስ ሠራተኞችና ለጎብኝዎች የደህንነት ስልጠና አሰጣጥና የስልጠና ተጨባጭ ዕቅድ<br>• ቅሬታዎችን ለማስተናገድ የሚረዳ የሂደት ዝርዝር<br>• ስለ እሳት አደጋ፣ የመጀመሪያ እርዳታና የእሳት ማጥፊያ ስልጠና አሰጣጥ<br>• ለአደጋ ጊዜና ከድንገተኛ አደጋ የማምለጫ ሂደቶች ዕቅድ<br>• አደጋዎችን ሪፖርት ለማድረግና ለመመርመር የሚረዳ አስገዳጅ መመሪያ<br>• ደህንነትን ለመፈተሽ ተብለው የተዘጋጁ ዕቅዶች<br>• የፋብሪካው የተጠያቂነት መድህን ቅጅ ወይም ዝርዝር ማጣቀሻ ናቸው፡፡<br>የደህንነት ፖሊሲው ለሠራተኞችና ለጎብኝዎች በቀላሉ ሊገባ በሚችል መልኩ በመደበኛነት ሊከለስ ይገባዋል፡፡ |

***የደህንነት ምርመራዎች፡*** ምርመራዎች የደህንነት አደጋዎችን መለየት እና የሊድ አሲድ ባትሪ መልሶ ዑደት ፋብሪካው ውጤታማና አስተማማኝ የደህንነት ስርዓት እንዳለው ግምገማ ማቅረብ አለባቸው::.

መርማሪው የአደጋ መዝገቦችንና የተዘለሉ ሁነቶችን በመተንተን ያለውን የደህንነት ስርዓት ክፍተት መለየት አለበት:: ምርመራዎች ስለፋብሪካው አሰራርና ስለደህንነት ፖሊሲው እውቀት ባላቸውና በሰለጠኑ ሰዎች መካሄድ አለባቸው:: አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ገለልተኛ የሆኑ መርማሪዎች ከውጭ መቀጠር አለባቸው::

በዓለማቀፍ የደረጃዎች ድርጅት የወጣው የሥራ ደህንነት ደረጃ (ISO 45001) ለደህንነት ምርመራው እንደ መመሪያ ሊያገለግል ይችላል:: ምርመራዎች ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ እንዲሁም አዳዲስ አሰራሮችና ማሽኖች በተጨመሩ ቁጥር በፋብሪካው ውስጥ መካሄድ አለባቸው:: ምርመራዎች የሠራተኞችን ትብብርና ፈቃደኝነት በማግኘት ፋብሪካው ዝግ ስለሚሆንበት ሂደትና የግል ደህንነት መጠበቂያዎችን መፈተሸን ማካተት ይገባቸዋል:: ማንኛውም የደህንነት አደጋ ተለይቶ የታወቀ እንደሆነ ለሠራተኞቹ ቀጥተኛና ፈጣን ግብረ መልስ ሊሰጣቸው ይገባል::

***የአደጋ መዝገቦች፡*** አደጋዎች እንደደረሱ ወዲያውኑ መመዝገብና መመርመር አለባቸው:: መዝገቦች በፋብሪካው ውስጥ አስፈላጊ የሆነ ማስተካከያዎችን ለማድረግ የሚረዱና ለወደፊቱ ሊከሰቱ የሚችሉ የአደጋዎችን፣ የአካል ጉዳቶችንና አላስፈላጊ የሆኑ ወጭዎችን ለማስወገድ የሚረዱ መሆን አለባቸው:: የአደጋውን ምንጭ ለማወቅና የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ይረዳ ዘንድ የአደጋውን ዓይነት በትክክል መግለጽ ጠቃሚ ነው:: ተቆጣጣሪዎችና የደህንነት ሠራተኞች ተገቢውን ስልጠና በማግኘት አደጋዎችን በትክክል ለመመዝገብ ዝግጁ መሆን አለባቸው:: ለችግሩ ምክንያት የሚሆኑ መንስኤዎችን በመተንተንና እውነታዎችን በማስቀመጥ ዝርዝርና እውነተኛ ሪፖርቶች እንዲቀርቡ ማበረታታት ከሰበብ ነፃ የሆነ የሥራ አካባቢ እንዲኖር ይረዳል:: የአደጋው ሪፖርት ማጠቃለያዎችና ተጨባጭ የማሻሻያ ምክረ ሐሳቦች የተጎዱ ክፍሎችን ለሚቆጣጠሩ የመስመር አመራሮች በትክክል መተላለፍ አለባቸው:: የማስተካከያ እርምጃዎችም ተግባራዊ መሆን አለባቸው::

***የደህንነት መነሻ ስልጠናዎች፡*** ስፊ የደህንነት መነሻ ስልጠና ጐብኝዎችና ሠራተኞች የሊድ አሲድ ባትሪ የመልሶ ዑደት ፋብሪካውን አቀማመጥ የምርት ሂደቶችን፣ ተያያዥ የሆኑ አደጋዎችን፣ ቀጥተኛ የሆኑ ተጋላጭነቶችንና በአግባቡ ደህንነታቸውን መጠበቅ የሚያስችሉ ባህሪያትን ለመተግበር የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነቶች ለማወቅ ይረዳል:: በስራ ቦታ ያሉ የደህንነት ምልክቶች ይብራራሉ፤ የግል የደህንነት መጠበቂያዎች ይብራራሉ እና ይሰጣሉ፤ የንፁህና የተበከሉ የስራ ክፍሎች ልዩነቶች ይብራራሉ፣ የአደጋና ከአደጋ መውጫ ሂደቶች ይገለፃሉ፤ ሕመም አደጋና የማይቀየር ክስተት እንዴት ሪፖርት እንደሚደረግ መመሪያ ይሰጣሉ::

መነሻ የደህንነት ስልጠና ተሳታፊዎች በስልጠናው ተሳታፊ መሆናቸውንና የተሰጠውን ስልጠና እንደተረዱት ማስተማመኛ ማስፈረም ያስፈልጋል::

***የአደጋ አሰሳዎች፡*** አደጋዎችን ሊያስከትሉ የሚችሉ ተጋላጭነትን ይቀንሳሉ:: ፋብሪካው የሠራተኞቹንና የጐብኝዎችን ደህንነት ለመጠበቅ ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያሉ:: በጤናና ደህንነት የአደጋ አሰሳዎች ውስጥ ስድስት ዋና ዋና ደረጃዎች አሉ:: (1) በእያንዳንዱ የስራ ሂደት ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ አደጋዎችን መለየት (2) የተወሰኑ የአደጋ ዓይነቶች ማንን፣ መቼና በምን ሁኔታ ሊጐዱ እንደሚችሉ መለየት (3) የአደጋውን የመከሰት ዕድልና የአደጋውን ከባድነት መገምገም (4) አደጋውን ለመቀነስ ወይም ለማስወገድ የሚረዱ እርምጃዎችን መለየት (5) የተጎዱ ሠራተኞችን ማሰልጠን (6) ለአደጋ አሰሳው አሰራር መደበኛ የሆነ ክለሳና ማስተካከያ ማድረግ::

ያገለገሉ የሊድ ዐሲድ ባትሪዎችን መቀበልና መሰበር፣ ሊድን ማቅለጥና ማጣራት እንዲሁም የጥገና ስራዎች፤ ባገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪ መልሶ ዑደት ስራ ውስጥ ከፍተኛ አደጋ ያለባቸው የስራ ቦታዎች ናቸው::

የባትሪ ዓይነቶችን መለየት፡ የተለያዩ የባትሪ ኬሚስትሪዎችን መቀላቀል በጣም የከፋና አደገኛ መዘዝ ያስከትላል:: በተለይም ያልተፍሞ አዮን ባትሪ በጣም ተቀጣጣይ በመሆኑ የከፋ ፍንዳታን ሊያስከትል ይችላል:: የኒኬል ካድሚየም ባትሪዎች ደግሞ በሊድ ማቅለጥና



The Federal Democratic Republic of Ethiopia ... Protection Authority

ማጣራት ላይ ጥራትን ያበላሻል፡፡ የባትሪ ኬሚስትሪዎች በመሰብሰቢያ ጣቢያዎች የተለዩ ቢሆንም እንኳን በመልሶ ዑደት ፋብሪካው ቦታም በስህተት ተቀላቅለው የመጡ ሌሎች የባትሪ ኬሚስትሪዎች ካሉ ለሁለተኛ ጊዜ መለየት አለባቸው፡፡

*የሥራ ፈቃድ፡* ፋብሪካው ወይም የተወሰኑ መሳሪያዎች እንዴትና መቼ እንደሚዘጉ ይወስናል፡፡
*መዝጋት፡* ፋብሪካውን ወይም የተወሰኑ የፋብሪካውን ክፍሎች መዝጋት ደህንነቱን ለጠበቀ ጥገናና ንፅህና ማካሄድ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ጥገና ወይም ፅዳት በሚካሄድበት ወቅት ይህ ስራ የሚከወንበት ማሽን እንዳይከፈት ለማድረግ ሰዎች በጥገና ላይ እንዳሉና እነማን እንደሆኑ የሚገልጽ ማስታወቂያ በመለጠፍ ክፍሉ መቆለፍ አለበት፡፡ ሥራው ሲጠናቀቅና ፋብሪካው ወደ መደበኛ ተግባሩ ለመመለስ ዝግጁ ሲሆን የጥገና ወይም የፅዳት ስራውን የሰራው ሰው ቁልፉን ይከፍታል፡፡ የትኛውን የፋብሪካ ክፍል፣ መሳሪያ ወይም ማሽን መቼ ለመዝጋት እንደታቀደ የሚያሳይ የተፃፈ መግለጫ መዘጋጀት አለበት፡፡ በመዝጋቱ ሂደት የሚሰሩት ሠራተኞች ኤሌትሪክ፤ ጋዝና እንፋሎት የመሳሰሉትን እንዴት ማቋረጥ እንደሚቻልና የአዘጋጉን ሂደት ስለመቆጣጠር መሰልጠን አለባቸው፡፡ የአየር ግፊት ያለባቸው ቱቦዎች፣ በኤሌትሪክ የተሞሉ መሳሪያዎችና በውኃ እንዲሁም በአየር ግፊት የሚሰሩ መሳሪያዎች የመዝጋት ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት በጥንቃቄ መያዝ ይገባቸዋል፡፡ የኤሌትሪክ ፊውዞችን ማስገወድና በውኃ ግፊት ለሚሰሩ መሳሪያዎች አቅርቦቱን ማቋረጥ ተጨማሪ ጥንቃቄን ማድረግም አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡ የኃይል አቅርቦታቸው የተቋረጡና ከጥገና በኋላ እንደገና እንዲገናኙ የተደረጉ መሳሪያዎች ወደ ስራ ከመግባታቸው በፊት በትክክል ስለመገናኘታቸው መፈተሽ አለባቸው፡፡

ለመዝጋት የምንጠቀምባቸው እንደ ቁልፍና መክፈቻ ያሉ መሳሪያዎች መቸ እንደተወሰዱና እንደተመለሱ በፊርማ ከሚያረጋግጥ መዝገብ ጋር ለዚሁ በተዘጋጀ ቋም ሳጥን ውስጥ በጥንቃቄ መቀመጥ አለበት፡፡

***የእሳት አደጋ ማስጠንቀቂያዎች፡*** ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎች የመልሶ ዑደት ስራ ባገለገሉ ባትሪዎች ውስጥ ከሚፈጠር ከፍተኛ ሙቀት፣ ከኃይል አስተላላፊ ሽቦዎች መገናኘት፤ ከነዳጅ እና ሌሎች ኬሚካሎች አጠቃቀም እና በስህተት ከተቀላቀሉ የሊቲየም አዮን ባትሪዎች የሚነሳ የእሳት አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡ የእሳት አደጋን ለመቀነስ የሚወሰዱ እርምጃዎች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡ (1) የእሳት አደጋ መነሻዎችን፣ ሊያደርሱ የሚችሉትን ጉዳትና እሳት ሊነሳባቸው የሚችሉትን አጋጣሚዎች መለየት (2) የአደጋ ጊዜ ምላሽንና አደጋ በደረሰ ጊዜ ከአደጋው ለመውጣት ጥሩ ቅንጅት ይኖር ዘንድ ቁልፍ የሆኑ መረጃዎችን በአካባቢው ላለ የእሳት አደጋ መከላከያ ማካፈል ናቸው፡፡ ተቀጣጣይ ይዘት ያላቸው የጋዝ ሲሊንደሮች ሲቀመጡ የጋዝ መውጫው ወደላይ በመሆን በሰንሰለት ታስረው ከመደርደሪያው ጋር መቆለፍ ይኖርባቸዋል፡፡ ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ ተሽከርካሪ ጐማ ባለው ማስቀመጫ ደህንነታቸው ተጠብቆ መቀመጥ ይገባቸዋል፡፡ የኤሌትሪክ ማከፋፈያ የያዙ ሳጥኖች አቧራ እንዳይገባባቸውና አላስፈላጊ የሆነ የኤሌትሪክ ግንኙነት እንዳይፈጠር በደንብ ተዘግተው መቆለፍ አለባቸው፡፡ ማቃጠያ ምድጃዎች የእሳት ነበልባልን እንዳይዛመት የሚያግድ መሳሪያና የአደጋ ማንቂያ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ሁሉም የሊድ አሲድ ባትሪ የመልሶ ዑደት ፋብሪካ ሠራተኞች የእሳት አደጋ መከላከያ ስልጠና መውሰድ አለባቸው፡፡ በፋብሪካው ውስጥ ሲጋራ ማጨስ በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡ ሁሉም የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያዎች በየስድስት ወሩ በእሳት አደጋ መከላከል ባለሙያ መፈተሽ አለባቸው፡፡ የሠራተኞች ዝርዝር በወቅቱ እንደሚኖራቸው የስራ ድርሻ መከለስ አለበት፡፡

***በአደጋ ጊዜ የመውጫ ዕቅድ፡*** በእሳት አደጋና የመርዝ ፍሰት በሚያጋጥምበት ወቅት ጊዜን ለመቆጠብና ነፍስንም ለማዳን ይረዳ ዘንድ የአደጋ ጊዜ መውጫ ዕቅድ፣ የመጀመሪያ እርዳታና የአደጋ ምላሽ ስርዓት ሁሌም ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡ በሁሉም የስራ አካባቢዎች የአደጋ ጊዜ መውጫ ዕቅዱና የአደጋ ምላሽ ለመስጠት ኃላፊነት የተሰጣቸው ሠራተኞች አድራሻ መለጠፍ አለበት፡፡ በአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታዎች ለአደጋ ተጋላጭነታቸው ዝቅ ያለ ሆኖ ከፋብሪካው ዋና የስራ ጣቢያ ውጭ መሆን አለባቸው፡፡ ሁሉም ሠራተኛ የመጀመሪያ እርዳታ አሰጣጥና የእሳት አደጋ መከላከል ስልጠናዎችን መውሰድ አለበት፡፡ ሠራተኞችን ለከፋ የአደጋ ጊዜ ዝግጁ ለማድረግ፣ ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪ የመልሶ ዑደት ፋብሪካው የእሳት አደጋ አወጣጥ ማንቂያዎችን በየሶስት ወሩ ማካሄድ አለበት፡፡ በአደጋ ጊዜ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች ምን ምን ናቸው፤ ለእሳት አደጋ መከላከያ የሚደውለው ማን ነው፣ ቁልፍ የአደጋ መውጫ መንገዶች የት ናቸው፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች የት ናቸውና ለእያንዳንዱ አደጋ

| | | |
|---|---|---|
| | | የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ምን ምን ናቸው የሚሉት ለሁሉም ሠራተኞችና ጐብኚዎች ግልጽ መሆን አለባቸው:: በአካባቢው ካለ የእሳት አደጋ መከላከል ጋር ጥብቅ ግንኙነት በመፍጠር በፋብሪካው ውስጥ ያሉትን መተላለፊያዎች፣ መሳሪያዎች፣ መከፈቻና መዝጊያዎች እንዲሁም ማብሪያ ማጥፊያዎች ማሳወቅ ይገባል::<br><br>*በእሳት አደጋ ጊዜ ሊኖር የሚገባ ጥንቃቄ:* ውኃ ከጋለ ብረት ጋር ሲገናኝ ፍንዳታን ስለሚያስከትል፣ የቀለጠ ብረት በሚኖርበት ጊዜ እሳትን ለማጥፋት በፍፁም ውኃን መጠቀም የለብንም:: የተሳካ የእሳት አደጋ መቆጣጠርን ለማካሄድ ትክክለኛውን የእሳት ማጥፊያ መምረጥ ቁልፍ ነው:: እንደ ወረቀት፣ እንጨት፣ ፕላስቲክ እና ለስላሳ የቤት ዕቃዎች ላሉ ጠጣሮች የመጀመሪያ ደረጃ (Class A) የእሳት ማጥፊያ መጠቀም እንችላለን:: እንደ ናፍጣ፣ ዘይትና ቤንዚን ያሉ ፈሳሽ ተቀጣጣዮች ሁለተኛ ደረጃ (Class B) የእሳት ማጥፊያ ያስፈልጋቸዋል:: የሊቲዬም አየን ባትሪዎች ተቀጣጣይ ፈሳሾች ስላላቸው የሁለተኛ ደረጃ የእሳት ማጥፊያን ይጠቀማሉ:: እንደ አሲታሊን፣ ሜቴን ወይም ፕሮፔን ያሉ ተቀጣጣይ ጋዞች ሶስተኛ ደረጃ (Class C) የእሳት ማጥፊያ ያስፈልጋቸዋል:: እንደ አሉሚንየም ማግኒዚየም፣ ሶድየም ወይም ሊቲየም ያሉ ተቀጣጣይ ብረቶች ደግሞ ቀጣዩ (Class F) የእሳት ማጥፊያ ያስፈልጋቸዋል:: |

**ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎች የመልሶ ዑደት ሂደት**

| | | |
|---|---|---|
| 4.1 | ባትሪ ሰበራ | ያገለገለ የሊድ አሲድ ባትሪ የተለያዩ ክፍሎች አሉት እነርሱም የፕላስቲክ ማቀፊያ፣ የሊድ ሰሌዳ መለያ፣ ብረታማ የሊድ ፍርግርግ፣ እርጥብ ሊድና ፈሳሽ አሲድ ናቸው:: ደህንነቱን የጠበቀና ውጤታማ የመልሶ ዑደትን ለማከናወን ከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ አውቶማቲክ መሰበሪያን በመጠቀም እያንዳንዱን የባትሪ ክፍል በመለየት የባትሪው ፍሳሽ እንዲሁም የሊድ ብናኞች በአግባቡ መያዝ አለባቸው::<br><br>ደህንነቱን ለጠበቀ የባትሪ ሰበራ የሚያገለግሉ ቴክኖሎጅዎችም፤<br>(1) የአሲድ ትነትና እንጥብጣቢዎችን በውስጥ የሚያስቀር በባትሪ መግቢያና መውጫዎች ላይ አሲድን የማያስተላልፉ መጋረጃዎች የተገጠመለት የባትሪ መጋዝ መጠቀም:: መጋዙ ማቀፊያውንና የባትሪ ማገናኛ ዋልታዎችን ከማስወገዱ በፊት ባትሪው ተበስቶ ሌሊቱን ሙሉ ፍሳሾቹ መውጣት አለባቸው:: ባትሪ በሚቆረጥበት ጊዜ የሚፈጠር የአሲድ ትነት በአየር ማናፈሻ መፅዳት አለበት:: የባትውን ማቀፊያ ከላይ ወደ ታች መገልበጥ ሰሌዳዎችን ለማላቀቅ ይረዳል::<br>(2) መዶሻ የተገጠመለት የመሰበሪያ ወፍጮን በውህ አማካኝነት ልየታን ከሚተገብር ሂደት ጋር መጠቀም:: ያገለገሉ ባትሪዎች በማጓጓዣ ችንጋው ስር እንዳይወድቁ በጎናቸው መቀመጥ አለባቸው:: ባትሪዎቹ ከማጓጓዣ ችንጋው ወደ ታች እንዳይንሸራተቱም የጎማ ዘንጎችን ከችንጋው ጋር ማያያዝ ይገባል:: ባትሪዎች በከፍተኛ ፍጥነት በሚሽከረከር መዶሻ ተሰብረው ይፈጫሉ:: መዶሻው ከፍተኛ ድምፅ ሊያወጣ ስለሚችል የድምፅ መጠኑ ከ 80 ዴሲብል በታች እንዲቀንስ አቃፊው ድምፅ የማያስተላልፍ መሆን አለበት::<br>መዶሻ፣ ቢላዋ፣ መጥረቢያና የመሳሰሉትን መሳሪያዎች በመጠቀም የሚካሄድ በሰው እጅ መሰበር ደህንነቱን የጠበቀ አይደለም:: ባገለገሉ ባትሪዎች የመሰብሰቢያ ጣቢያዎች ወይም በሚጓጓዙበት ጊዜ የባትሪ ሰበራ መካሄድ የለበትም::<br><br>በባትሪ ሰበራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች የጎማ ወይም የፕላስቲክ ሽርጥ፣ የጎማ ጓንት፣ የአሲድ ትነትን መምጠጥ የሚችል የብናኝ መከላከያ መተንፈሻ፣ የደህንነት መጠበቂያ መነጽሮች፣ አሲድን የሚቋቋሙ ቦት ጫማዎች፣ እጅጌያቸው ረጅም የሆኑ ቶታዎች፣ ጠንካራ ኮፍያና የጆሮ መከላከያ መልበስ አለባቸው:: |
| 4.2 | ሊድን ማውጣት | ሰልፈርን ማስወገድ:- በማቅለጥ ሂደት የሰልፈር ዳይኦክሳይድ ልቀትን ለማስወገድ ከባትሪው እርጥብ ውህድ ውስጥ ያለውን ሰልፈር ከማቅለጥ ሂደት በፊት፣ በማቅለጥ ሂደት ጊዜ እና ከማቅለጥ ሂደት በኋላ መወገድ አለበት::<br><br>(1) ከማቅለጥ በፊት:- ይህ መደረግ የሚችለው መዶሻ የተገጠመለት ወፍጮን ለባትሪ ሰበራ ለሚጠቀሙ ፋብሪካዎች ብቻ ነው (4.1ን ይመልከቱ):: ከወፍጮው |

የተሰበሰበው እርጥብ ሊድ ከካልሲየም ካርቦኔት ወይም ከሶዲየም ካርቦኔት ጋር ተቀላቅሎ ካልሲየም ፎስፌት (ጅፕሰም) ወይም ሶዲየም ሰልፌት ይሰራበታል፡፡ ጅፕሰም ደግሞ የሊድ ጥፍጥፍ በሚሰራበት ጊዜ ለማቀዝቀዝ፣ የቤት መለሰኛ ለመስራት እንዲሁም ስሚንቶ በሚሰራበት ጊዜ ለማጠናከሪያ ይጠቅማል፡፡ ሶዲየም ሰልፌት ለብርጭቆ ስራና ጥራት ያለው ወረቀትን ለማምረት ባለው የስራ ሂደት እንደ ግብአት ይጠቅማል፡፡ ከማቅለጥ በፊት ሰልፈርን ማስወገድ በፋብሪካው የአየር ማስተንፈሻ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ዝገት ለመቀነስ፣ ከማቃጠያ የሚወጣ የዝቃጭ መርጋትን ለመቀነስና አደገኛ ያልሆኑና ሊሸጡ የሚችሉ ምርቶችን ለማግኘት ይረዳል፡፡

(2) በማቅለጥ ሂደት፡- ውድ ያልሆኑ የብረት ቁርጥራጮችን በመጠቀም ከ95% በላይ የሆነ ከፍተኛ ውጤት የሚያስገኝ ሰልፈርን ማስወገድ ይቻላል፡፡ በዚህም ሂደት ፌረስ ሰልፋይድ ይመረትና የዝቃጩን መጠን ይጨምረዋል፡፡ ይህን ሂደት ሶዲየም ካርቦኔት በመጨመር የበለጠ ውጤታማ ማድረግ ይቻላል፡፡ የሚወጣውን ብናኝ ለማጠራቀም የብረት በርሜሎችን መጠቀም ይቻላል፡፡ ብናኝ ተሞልተው የታሸጉ በርሜሎችን በተሽከርካሪ ማቃጠያ ውስጥ በማስገባት የአደገኛ ቆሻሻ ተረፈ ምርቶችን በመልሶ ዑደት መጠቀም ይቻላል፡፡

(3) ከማቅለጥ በኋላ፡- የመጨረሻ የሰልፈር ዳይኦክሳይድ ቅንጣቶችን እስከ 99% ማስወገድ ይቻል ዘንድ በማጣሪያው አቅራቢያና ከጭስ መውጫው በፊት መፈቅፈቂያ መግጠም ይቻላል፡፡ ይህ ያለው የብረት ጋን የሶዲየም ካረቦኔት ወይም የካልሲየም ካርቦኔት አልካላይ ከላይ እየተረጨበት ካርቦንዳይ አክሳይድን የሚሰራ ነው፡፡ የካልሲየምና የሶዲየም ሰልፌት ይዘቶች በውህዱ ውስጥ ሲንሳፈፉ ጨዎች ተለይተው እንደተረፈ ምርት ሊሸጡ ይችላሉ፡፡

መፈቅፈቂያው፣ የአንደኛውና የሁለተኛው ስርዓት ካልሰራ እንደመጠባበቂያ ይሆናል እንጅ እንደ መጀመሪያ አማራጭ አያገለግልም፡፡ ሰልፈርን የማስወገድ ስራ ውጤታማ እንዲሆን የ1+3፣ የ2+3 ወይም የሦስቱም ደረጃዎች ቅንጅት አብሮ መስራት አለበት፡፡

የቱንም ዓይነት የሰልፈር ማስወገድ ሂደት ላይ የሚሰሩ ሰራተኞች የእግር ጣቶችን ከአደጋ የሚከላከሉና አሲድ የማያስተላልፉ ቦት ጫማዎችን፣ ረጅም እጅጌ ያላቸው ቱታዎችን፣ ብናኝን የሚከላከሉ የመተንፈሻ መሳሪያዎችን፣ የመከላከያ መነፅሮችንና ጠንካራ ኮፍያዎችን የመሳሰሉ የግል ደህንነት መከላከያ ትጥቆችን መልበስ አለባቸው፡፡ ለስራ ሂደት (1) እና ለስራ ሂደት (3) ሰራተኞች ጠንካራ ጓንቶችን ማድረግ አለባቸው፡፡ ለስራ ሂደት (2) ሰራተኞች በማቃጠያ ቦታ መጠቀም የሚቻልን ሙቀት የሚቋቋም ጓንት ማድረግ አለባቸው፡፡

ባገለገሉ ባትሪዎች ውስጥ ካሉ ሊድ ከያዙ ክፍሎች ውስጥ ብረታማ ሊድ ለማግኘት በሚደረገው የማቅለጥ ስራ፤ ሰራተኞቹና በአካባቢው ያለው ማህበረሰብ ሊገጥመው የሚችለውን የሊድ ተጋላጭነት መቀነስ ይቻል ዘንድ

አካባቢ ጥበቃን ማዕከል ያደረገ የማቃጠያ ቴክኖሎጅን መጠቀም የገባል፡፡ ተገቢው ቁጥጥር ካልተደረገለት በስተቀር በማቅለጥ የሚከናወነው መልሶ ዑደት በሊድ የተበከለ ነበልባል፣ ብናኝና ሰልፈር ዳይኦክሳይድ በማመንጨት ወደ ውጭ ሊለቅ ይችላል፡፡ ተገቢ የሆነ ማቃጠያን መጠቀም ከተቻለ፤ መርዛማ የሆኑ ነገር ግን ጥቅም ያላቸውን ተረፈ ምርቶች በአግባቡ በመልሶ ዑደት መጠቀም ይቻላል፡፡ የማቃጠያ ቴክኖሎጅው የሚከተለውን መስፈርት መሰረት አድርጎ መመረጥ አለበት፡፡

- አካባቢ ጥበቃን ማዕከል ያደረገ አፈፃፀም
- በስራ ሂደቱ የሚካተቱት የብረትና ሌሎች ግብዓቶች መጠን
- የሚያስፈልጉት ግብዓቶች ዓይነት እና
- የሚጠቀመው የነዳጅ ዓይነት

በብዛት የተለመደው የማቃጠያ ዓይነት ከ500-1100 ዲግሪ ሴልሺየስ በሆነ ሙቀት ፍርግርግ ብረቶችን፣ እርጥብ የባትሪ ውህዶችን፣ እንደ ዝቃጭና ብናኝ ያሉ ተረፈ ምርቶችን ሊያቀልጥ የሚችል ተሽከርካሪ ማቃጠያ ነው፡፡ ረጅም ተሽከርካሪ ማቃጠያ በዓመት ውስጥ ከ30,000 እስከ 40,000 ሜጋ ቶን የገለገሉ ባትሪዎችን ያቃጥላል፡፡ ተሽከርካሪ ማቃጠያ ሁሉንም ተረፈ ምርቶች ለመልሶ ዑደት በማዋልና የማቅለጥ ሁኔታዎችንና ልቀቶችን በቀላሉ ለመቆጣጠር በማስቻል ከዚህ ቀደም በብዛት ጥቅም ላይ ይውል ከነበረው ማቃጠያ የተሻለ ነው፡፡

ተሽከርካሪ ማቃጠያ ውጭው በብረት የተለበደ ሲሆን፣ ውስጡ ደግሞ በማግኒዚየም ክሮም አንፀራቂ የተሸፈነ ነው፡፡ በርሜሉ የተጣበቀ ሆኖ ወይም በሁለት አቅጣጫ በዘንግ ተንጠልጥሎ ሊሽከረከር ይችላል፡፡ የተጣበቀ ዘንግ የሚጠቀም ከሆነ፣ ማቃጠያው ከኋላ

መሆን አለበት፡፡ የተንጠለጠለ ከሆነ ግን ማቃጠያው ከፊት ለፊት ይሆናል፡፡ ወደ ማቃጠያው የሚገባው ቁስ በአውቶማቲክ መመገቢያ ወይም ከርቀት ሊቆጣጠሩት በሚችሉት መንገድ የሚሰራ መመገቢያ መሆን አለበት፡፡ የቀለጠው ሊድና ዝቃጩን ለመቅዳት ከተዘጋጀበት ቧንቧ ላይ የሚቀዳ ሲሆን፤ ተንጠልጣይ ዘንግ የሚጠቀም ማቃጠያ ከሆነ ደግሞ ማቃጠያው በጥንቃቄ ወደፊት ዘንበል እንዲል ተደርጎ በበሩ በኩል እንዲቀዳ ይሆናል፡፡

ሌሎች የማቃጠያ ዓይነቶች (ለምሳሌ ኢሳስሜልት/ኤዩስሜልት እና ከታችኛው ክፍሉ አሳትን የሚቀበል ማቃጠያ) ዘመናዊ ንድፍን ተከትለው ልቀትንም የሚቆጣጠሩ ከሆነ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡

በቀጥታ ነበልባል የሚያቃጥልና ሙቀትን በማስተጋባት የሚያቃጥሉት መሳሪያዎች ጥቅም ላይ መዋላቸው ስለቆመ መፈቀድ የለባቸውም፡፡

የተበከለ አየር ወደማጣሪያ ገብቶ እንዲጣራ ሁሉም ዓይነት ማቃጠያዎች ዙሪያቸው ታሽጎ ማስተንፈሻ ሊኖራቸውና በውስጣቸው ባለው ክፍተት ሁሉ የሚወጣውን የተበከለ አየር ሰብስቦ የሚያወጣ ከለላ ሊገጠምላቸው ይገባል፡፡ ማቃጠያው ውስጥ የሚቃጠሉ ቁሶች በሚገቡበትና የማቃጠል ስራው በሚከናወንበት ጊዜ ሁሉ ብናኝና ነበልባሉን መያዝ ይቻል ዘንድ የማስተንፈሻ መሳሪያው ክፍት መሆን አለበት፡፡

## ወደ ማቃጠያው የሚገቡ ቁሶችን ማዘጋጀት

ወደ ማቃጠያው የሚገቡ ቁሶችን መለየትና በትክክል ማዘጋጀት የማቃጠያውን የስራ ድግግሞሽ የሚቀንስ ሲሆን የማምረቻ ጊዜውንም ይጨምራል፡፡ ወደ ማቃጠያው የሚገቡ ቁሶች ለስላሳ የሊድ ቁርጥራጮችን፣ ፍርግርግ ብረቶችን፣ እርጥብ ሊድ ኦክሳይድን፣ የባትሪ ሰሌዳዎችን፣ ቃጠሎን የሚቀንሱ ቁሶችን፣ ፍሳሽ እንዲኖርና ሰልፈርን ለማስወገድ የሚረዱ እነ ሶዲየም ካርቦኔትና እንደ ብረት ያሉ ቁሶችን ሊይዝ ይችላል፡፡ ተገቢ የሆነ የሚቃጠሉ ቁሶች ዝግጅት የሊድ ብክለት ተጋላጭነትን ይቀንሳል፡፡ ወደ ማቃጠያው የሚገቡት ቁሶች በሚዘጋጁበት ቦታ ያሉ ሰራተኞች ሁሉ ቢያንስ ፒ2፣ ከተቻለ ደግሞ ፒ3 የብናኝ መከላከያ ያለው መተንፈሻ መልበስ ይኖርበቸዋል፡፡ የዐይን መከላከያ መነፅሮች ወይም ፊትን የሚሸፍን መስተዋትና ጠንካራ ኮፍያም መልበስ ይኖርባቸዋል፡፡ የእግር ጣቶቻቸውን በደንብ መከላከል የሚያስችሉ ጫማዎችን፣ ረጅም እጅጌ ያላቸው ከጥጥ የተሰሩ ቱታዎችንና የሪገር ጓንቶችን መልበስ አለባቸው፡፡ የቱታዎቹ ሱሪዎች ከቦት ጫማው በላይ ሆነው መለበስ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም የሊድ ቅንጣቶች በጫማ ውስጥ ገብተው እንዳይበክሉ ይከላከላል፡፡

ወደ ማቃጠያው የሚገቡትን የቁሶች ዝግጅት ቢያነስ የሚከተሉትን መሰረታዊ ሀሳቦች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

- እንደ ሊድና የብረት ቁርጥራጭ ያሉ ቁሶች ለብቻ መከማቸት አለባቸው
- የማከማቻ ቦታው ዝግ የሆነ ግንባታ ውስጥ ሆኖ የሊድ ቅንጣቶች ወደ ማጣሪያው ብቻ እንዲገቡ ተቃራኒ የሆነ የአየር ግፊት ሊኖረው ይገባል፡፡
- ካገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎች የመልሶ ዑደት የሚወጡ ተረፈ ምርቶች በታሸገ ማጠራቀሚያ ወይም ወደ ማቃጠያው የሚመግብ መያዣ ውስጥ መጠራቀም ይኖርባቸዋል፤ የሚይዙትም መያዝ ከሚችሉት ልክ በላይ መሆን የለበትም፡፡
- በማቅለጥ ጊዜ ሰልፈርን ማስወገድ የሚከናወን ከሆነ፤ (ዘዴ 2ን ማለት ነው፤) በትክክል የተመዘነ ብረት ወደ ማቃጠያው መጨመር አለበት፡፡
- ቁሶች በሰው እጅ የሚዘጋጁ ከሆነ ሰራተኞቹ ብናኝን የሚከላከል የግል ደህንነት መጠበቂያ መሳሪ መጠቀም አለባቸው፡፡

በመሠረቱ የእነዚህ ቁሳቁሶች አያያዝ እንደ መኪና በመሳሰሉ በተዘጋ ጋቢና በሚዘወሩና የተጣራ አየር አቅርቦት በተገጠመላቸው አውቶማቲቾ መሳሪያዎች መከናወን አለበት፡፡ የፊትለፊቱ መስታወት የማይሰበር ሆኖ ሙቀትን የሚቋቋም መሆን አለበት፡፡

በባትሪ መጋዝ ለተዘጋጁ የሚቃጠሉ ቁሳቁሶች:

- ከፍርግርግ ብረቶች ላይ ያሉትን እርጥብ ውህዶች አለማንሳት
- የሰሌዳ መለያያውን አለማንሳት
- የባትሪ ማገናኛ ዋልታዎች ከባትሪ ሽፋኑ በሚነሱበት ጊዜ በቀጥታ ወደ ማጣሪያ ድስቱ መገልበጥ ይቻላል፡፡

መዶሻ ከተገጠመለት ወፍጮ ለሚወጡት የሚቃጠሉ ቁሶች

- እርጥበት ያላቸውን ውህዶች ከፍርግርግ ብረቱ ማፅዳት፡፡ ፍርግርግ ብረቶች

| | | |
|---|---|---|
| | | በቀጥታ ወደ ማቅለጫው ሊጨመሩ ይችላሉ:: ወይም በዓይነት በዓይነት በየተራ እርጥብ ውህዱንና ፍርግርግ ብረቱን ወደሚያቀልጥ ማቃጠያ ሊጨመሩ ይችላሉ:: ዕርጥብ ውህድ የሆነውን የባትሪ ክፍል ለብቻው ማቅለጥ የተጣራ ሊድ ስለሚሰጥ ተጨማሪ ማጣራት አይፈልግም::<br>• እርጥበት ካለው የባትሪ ውህድ ውህንና ሰልፈርን ማስወገድ:: መጭመቅና ማጣራት ውህውን ያስወግዳል:: ሰልፈርን ደግሞ ከላይ በተገለፀው ሰልፈርን የማስወገድ ዘዴ ማስወገድ ይቻላል::<br>• በዚህ ዓይነት እርጥብ የባትሪ ውህድን የማቅለጥ ሂደት ውስጥ ምንም ዓይነት ተረፈምረቶች (ለምሳሌ ዝቃጭና ብናኝ) መቀላቀል የለባቸውም::<br>• በባትሪ እርጥብ ውህድ ማቃጠያው ውስት በፖሊኤቲሊን የብርጭቆ ቃጫ የተሰራ የሰሌዳ መለያ ሊጨመርበት ይችላል፤ ይህም የሊድ ምርቱን አይበክልም::<br>የሚቃጠሉ ቁሶችን ወደማቃጠያው ማስገባት በከፊል አውቶማቲክ መሆን አለበት:: ከፍተኛ የሊድ ብክለት ተጋላጭነትና የፍንዳታ አደጋ ስላለው ፈፅሞ በእጅም ሆነ በአካፋ ሊሰራ አይገባውም:: የፍንዳታ አደጋን ለመቀነስ የሚቃጠሉ ቁሶች ቢያንስ 5% የእርጥበት ይዘት ሊኖራቸው ይገባል:: ማቃጠያውም ከአቅሙ በላይ መሞላት የለበትም:: ዳዮክሲንና ፊዩራን እንዳይፈጠሩ ለመከላከል ቁሶች ወደ ማቃጠያው በሚገቡበት ጊዜ ቢያንስ 450 ድግሪ ሴልሺየስ ሙቀት ሊኖረው ይገባል:: ለመያዝ የሚያስቸግሩ የሊድ ብናኞችና ነበልባል በመፍጠር ጊዜውን ያልጠበቀ ያልተጣራ ብረት ሊፈጠር ስለሚችል በማጣሪያው ድስት ውስጥ ፍርግርግ ብረቶች እንዲቀልጡ መጨመር የለባቸውም:: ከዚህ ይልቅ እንዲህ ያለ የማቅለጥ ሂደት በዝቅተኛ ሙቀት በሚሰሩ በተለመዱት ተሽከርካሪ ማቃጠያዎች ወይም ብክለትን የሚያስወጣ ማስተንፈሻ በተገጠመለት ልዩ ማቅለጫ ውስጥ ሊከናወን ይችላል::<br><br>ቁሶች ወደ ማቃጠያ ውስጥ በሚገቡበት ጊዜና ቃጠሎው በሚከናወንበት ጊዜ በማቃጠያው ስር የሚፈጠር የብናኝ ልቀት ሙሉ በሙሉ ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል:: በዚህ የስራ ሂደት የሚኖረውን ሙቀት ለመቆጣጠር የደህንነት ቅድመ ጥንቃቄዎች ሊኖሩ ይገባል:: ቀላጭ ቁሶች መሬት ላይ በሚወድቁበት ጊዜ በተለየ የቤት አያያዝ ስርአት በመደበኛነት ሊነሱ ይገባል:: እንደ ኤዩስሜልት ያሉ ማቃጠያዎች ከርቀት መቆጣጠር የሚቻልና ያልተቋረጠ የቁሶችን ወደ ማቃጠያው መጨመር የሚያረጋግጥ አውቶማቲክ ስርዓት ሊኖራቸው ይገባል::<br><br>እንደ ተሽከርካሪ ማቃጠያ ያሉ ሌሎች ማቃጠያዎች ተራዉን እየጠበቀ የተለያዩ ቁሶችን የማቃጠል ሂደትን ይከተላሉ:: ልቀትንና የኃይል አጠቃቀምን ለመቀነስ ይረዳ ዘንድ በየተራ የሚካሄድ ማቃጠል በርቀጥ ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል:: በፍጥነት ቁሶችን ወደ ማቃጠያው መጨመር የማቃጠያ የዑደት ጊዜውን ይቀንሳል:: በዓመት ከ12,000 ሜጋ ቶን በላይ ለሚያቃጥሉት አውቶማቲክ የሆነ የሚቃጠሉ ቁሶችን ወደ ማቃጠያው መጨመሪያ መሳሪያ መጠቀም ገንዘብ ቆጣቢ ነው:: ሰራተኞቹ ተያያዥ ከሆነ የፋብሪካው ልቀቶች ብክለት እስከተጠበቁ ድረስ ለትንንሽ ማቃጠያዎች ከፊል አውቶማቲክ የሆነ የቀላጭ ቁሶች መጨመሪያ መጠቀም ይቻላል:: |
| 4.3 | ሊድን ማቅለጥና መቅዳት | ሊድን ማቅለጥ መካሔድ ያለበት በቂ የሆነ የደህንነትና የንፅህና ተግባራት ቁጥትር ባለበት ሁኔታ ብቻ ነው:: ሰራተኞች ከሊድ ነበልባልና ከብናኝ ልቀቶች ብክለት መጠበቅ አለባቸው:: በስራ ቦታ ያለ የተቀላቀለ የሙቀት፣ የነዳጅና አንዳንድ ጊዜም የኦክስጅን መጠን የተለየ ጥንቃቄ ይፈልጋል:: ሊታዩ የሚገቡ የደህንነት ህጎችም:<br>• ከእያንዳንዱ የስራ ሂደት ጅማሬ በፊት ማቃጠያው እከል እንዳይገጥመው የሚያደርገው መሳሪያ በትክክል መስራቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ይህም ያልተቃጠለ ነዳጅ ወደ ጋለ ማቃጠያ እንዳይገባና ማቃጠያው በማይሰራበት ጊዜ የኦክስጅን ግፊት እንዳያገኝ ያደርገዋል::<br>• በማቅለጥ ጊዜ ፍሳሽ ከተደፋ ፍሳሹን ለመቆጣጠርና እሳትን ለማጥፋት አሸዋ መጠቀም አለብን:: በፍሳሹ ላይ ፈፅሞ ውህ መርከፍከፍ የለበትም::<br>• ነበልባሎችና ብናኞች በትክክል እንዲያዙ፣ በማስተንፈሻ ስርዓት ውስጥ ያሉ የአየር ማቀዝቀዣዎች በትክክል መስራታቸውን ማረጋገጥ ይገባል::<br>• የሰልፈር ዳይኦክሳይድና የካርቦን ሞኖኦክሳይድ በቀዳዳዎች የማምለጥ አደጋ ሊኖር ስለሚችል የማቅለጥ ስራ በሚካሄድበት ጊዜ በጣሪያው ላይ ወይም በጭስ መውጫው እናት አካባቢ የፍተሻ ስራ መከናወን የለበትም::<br>• ለተገለባባጭ ማቃጠያ የሙቀት ብክነትን ለመቀነስ በሚሰራበት ጊዜ የሚኖረውን ልቀት ለመያዝ በአየር ማስተላለፊያው ውስጥ የሚወጣውን የልቀጥ ደረጃ በጥንቃቄ መቆጣጠር አስፈላጊ ነው:: |

- ሙቀትን መከታተል ጠቃሚ ነው:: የማቅለጥ ስራው በዝቅተኛውና በከፍተኛው ሙቀት መጠን መካከል መከናወኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: አነስተኛ የሆነ የሙቀት መጠን ከፍተኛ የሊድ ይዘት በዝቃጩ ውስጥ እንዲኖር ያደርጋል:: ከፍተኛ የሙቀት መጠን ደግሞ የሊድ ይዘት መጠኑ የበዛ ብናኝ ወደ ብናኝ ማጠራቀሚያው እንዲሄድ ያደርጋል::
- የማቅለጫ ሙቀቱ በማቅለጫ ውስጥ ለገቡት ድብልቅ ቁሶች በሚመጥን መልኩ መቀነስ አለበት:: ለምሳሌ በተሽከርካሪ ማቃጠያ ውስጥ ለሶዳ ብረት ደረጃ በሚመጥን ስርዓት ሙቀቱ ሊቀንስ ይችላል:: ሶዲየም ካርቦኔትና ብረትን መጨመር እስከ 95% ሰልፈርን ያስወግዳል፤ በውስጥ ያሉ መሳሪያዎችን መበላሸት ይቀንሳል፤ እንዲሁም የነዳጅ ፍጆታን ይቀንሳል::

- በማቅለጥ ሂደት የእይታ ፍተሻ በሚካሄድበት ጊዜ የሚከተሉትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡
  - ✓በማቃጠያው አካባቢ ከሰለጠኑና ለስራው ከተመደቡት ሰራተኞች ሌላ ሰው መገኘት የለበትም
  - ✓የማቃጠያው የውጪኛው ልባድ በውስጥ ያለውን የሙቀት ተከላካይ ሽፋን መበላሸት ተከትሎ ሙቀት ወደውጭ እንዲያመልጥ ማድረግ የለበትም::
  - ✓ከአየር ማስተላለፊያውና ማቃጠያው የሚወጣ ልቀት መኖር የለበትም፤ ከብናኝ ማጠራቀሚያው የሚለቀቀ ብናኝም ሊኖር አይገባም::
  - ✓የብናኝ ማጠራቀሚያው ብዙ ለማጠራቀም አቅም ያለው መሆኑን ማረጋገጥና ተተኪ ማጠራቀሚያዎች መኖራቸውንም ማረጋገጥ::
  - ✓በብናኝ ማጠራቀሚያው መግቢያና መውጫ ያለውን ግፊት መመዝገብና የግፊት ልዩነቱ ከንድፍ ወሰኑ የበለጠ ከሆነ እንዲፀዳ ማድረግ::
  - ✓በአደጋ ጊዜ መውጫና በመረማመጃ ቦታዎች ፍሳሽና ቆሻሻ አለመኖሩን ማረጋገጥ
  - ✓ማቅለጡ ከተጠናቀቀ በኋላ የመቅዳት ስራን ለማከናወን የሚረዱ መሳሪያዎችና የግል ደህንነት መጠበቂያዎች ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ
  - ✓ማጠቢያዎችን ጨምሮ የቀለጡ ብረቶችንና ዝቃጮችን የሚቀበሉ ትኩስ ይዘቶችን ሲቀበሉ እንዳይሰነጠቁ ቀድመው መሞቅ ይኖርባቸዋል

ሰራተኞችን ከጉዳት ለመጠበቅና ልቀትን ለማስወገድ ወይም ለመያዝ፤ የቀለጠውን መቅዳት በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊከናወን ይገባዋል:: የማቅለጥ ሂደቱ በተሳካ ሁኔታ የመጀመሪያ ደረጃ ሊድ እንዲያስገኝ በከፍተኛ የሙቀት መጠን ይከናወናል:: ከፍተኛ የሙቀት መጠን ስለሚፈልግ፤ ይህን ዓይነት የማቅለጥና ማጣራት ሂደት ከተራ ማቅለጥ ሂደት የተለየ ጥንቃቄ ይፈልጋል ፤ (ለዚህም ምሳሌ የሚሆኑት ስስ የሆነ የመጀመሪያ ደረጃ የሊድ ቁርጥራጭ፣ በውሀ ውስጥ የሚያልፉ ሽቦዎች፣ ካገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎች የተገኙ የፀዱ ፍርግርግ ብረቶች ናቸው)::

መቅዳትን በተመለከተ፤ በሰው እጅ መቅዳት የተለመደ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን አውቶማቲክ ወይም በርቀት ቁጥጥር የሚደረግበት አቀዳድ ተመራጭ ነው:: በሰው እጅ የሚከናወኑ መቅዳቶች ሚዛናቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ እጀታ ያለው ብረት ከማቃጠያው ጋር አብሮ ሊሰራ ይገባዋል:: የተራ ማቅለጫና የተጣራ ማቅለጫ የመቅጃ ክዳኖች ሲከፈቱና ሲዘጉ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት:: የመቅጃውን ክዳን ለማሸግ የተለየ ዓይነት ሸክላ ጥቅም ላይ መዋል አለበት:: በተመሳሳይ ሁኔታ የመቅጃ ክዳኑ በቀላሉና በፍጥነት የሚከፈት መሆን አለበት:: ካዘነበለ ተሽከርካሪ ማቃጠያ መቅዳት አያስፈልግም:: ነገር ግን ማቃጠያውን ወደ ፊት ዘንበል በማድረግ የቀለጠው ሊድ ወደ ተፈለገበት እቃ እንዲገለበጥ ማድረግ ይቻላል::

### የቀለጠ ሊድና የዝቃጭ አያያዝ

ጥራት ያለው የማቅለጥ ሂደት ከተከናወነ በኋላ የቀለጠው ብረት ወደ ጋለ ቅርፅ መስጫ መገልበጥ አለበት:: ይህም ሊኖር የሚችለውን የግለት ልዩነት በማጥበብ ሊፈጠር የሚችለውን የብናኝ ልቀት፣ ተዛማች ነበልባልና ይህንም ተከትሎ ሊከሰት የሚችልን የድስት መሰንጠቅና የሊድ መደፋት፤ እንዲሁም በሰራተኞች ላይ ሊደርስ የሚችልን ጉዳት መቀነስ ይቻላል:: ተቀባይ የቅርፅ መስጫዎችን ቀድሞ ለማጋል ከ400 – 500 ዲግሪ ሴልሺየስ የሆነ የቀለጠ ብረት መሙላት ይቻላል:: የተሞላውም ብረት ከቀዘቀዘ በኋላ በሞተር ግፊት ወደ ማጣሪያው ሊገባ ይችላል:: በሞተር ግፊት ማስተላለፍ ካልተቻለ የጋለው ብረት አንፀባራቂ ልባድ ወዳላቸው የብረት ቅርፅ መስጫዎች ወይም እንስራዎች ተገልብጦ ከ1 – 2 ቶን

| | | |
|---|---|---|
| | | የሚሆኑ የሊድ ጉራጆችን መስራት ይቻላል፡፡ የሊድ ነበልባል ከ500 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ ባለ ሙቀት ውስጥ ስለሚፈጠር፤ የጋሉት የሊድ ጉራጆች በሚቀዘቅዙበት ቦታ ይህን ሙቀት ማውጣት በሚችል የአየር ማስተንፈሻ ስር መሆን አለበት፡፡ ሊድ በሚቀዳበት ሰዓትም የአየር ማስተንፈሻው በከተኛው ኃይሉ ስራ ላይ መዋል አለበት፡፡ ብብናኝና ነበልባል አመንጭ ቦታዎች የሚኖረው የአየር እንቅስቃሴ ፍጥነት 1 ሜትር በሰከንድ መሆን አለበት፤ በማስተንፈሻው መተላለፊያ ደግሞ 7 ሜትር በሰከንድ መሆን አለበት፡፡ በሚቀዳበት ጊዜ ውጤታማ የሆነ የአየር ማስተንፈሻ ስርዓት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም አየር ወደ አየርና ብናኝ ማጣሪያው መተላለፍ አለበት፡፡<br><br>ወደ ማጣሪያው ድስት በማሽን ማጓጓዝን ለማሳለጥ ይረዳ ዘንድ በሚቀዘቅዙበት ጊዜ በቀለጠው የብረት ጉራጅ ውስጥ መልሀቅ ሊገባበት ይገባል፡፡<br><br>ዝቃጭንም ለቀለጠው ብረት በተደረገው መልኩ በማቀዝቀዝና በመቅዳት ከ1-2 ቶን ጉራጆች እንዲሰራ መደረግ አለበት፡፡ ሆኖም ግን አንዳንድ ዝቃጮች በተለይም ከተሽከርከሪያ ማቃጠያ የሚወጡት ከፍተኛ የሆነ የሊድ ይዘት ካላቸው ፍንዳታን በመፍጠር ሊድ የያዘ ልቀትን የሚጥር ቃጠሎ ያስነሳሉ፡፡ ካርቦን ዳይኦክሳይድ ወይም በአረፋ የሚሰራ የእሳት ማጥፊያ በአጠገቡ መኖር እና የዝቃጭ ማቀዝቀዣ ስርዓቱ በአየር ማስተንፈሻ መደገፍ አለበት፡፡ የቀዘቀዘ ዝቃጭ እሳትን አያስነሳም፡፡<br><br>ከማቅለጥ ሂደቱ በኋላ፣ የቀለጠው ሊድ በቀጥታ ወደ ቅርፅ መስጫው ብረት ወይም ወደ ማጣሪያው ድስት ሊገለበጥ ይችላል፡፡ በዚህም ጊዜ ሙቀቱ ከ500 ዲግሪ ሴልሺየስ በታች ስለሚወርድ ብክለትን አስወጋጅ የአየር ማስተንፈሻ መጠቀም አያስፈልግም፡፡ መቅዳቱ በእርቀት የማይካሄድ ከሆነ እንደ የደህንነት መጠበቂያ ኮፍያ፣ ኤን 95/ ኤች ኤፍ ፒ2 መተንፈሻዎች፣ የዓይን መከላከያ መነፅሮች፣ እጅጌው ረጅም ከጥጥ የተሰራ ቱታ፣ የእግር ጣቶችን ከአደጋ ለመጠበቅ የሚረዳ ብረት ወይም የካርቦን ቃጫ ያለው ቦት ጫማ፣ ከቆዳ የተሰራ ሽርጥና የጋለ ነገርን መያዝ የሚያስችል ጓንት መጠቀም ግዴታ ነው፡፡ |
| 4.4 | ማጣራት እና ማዋሀድ | ሊድን ማጣራትና ማዋሀድ በመልሶ ዑደት ፋብሪካው ውስጥ ሊሰራ የሚችል አንደኛው አማራጭ ስራ ነው፡፤ የስራ ሂደቱ ያልተጣሩ የሊድ እንኳሮችን ወደተጣራ ሊድ የለውጣቸዋል፡፡ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎችን መልሶ ዑደት የሚሰራ ፋብሪካ ያልተጣሩ የሊድ እንኳሮችን በማምረት ለሌሎች ፋብሪካዎች ሊዱን እንዲያጣሩት ማስተላለፍ ይችላል፡፡ የተጣራ ሊድ (99.99% ጥራት ያለዉ) እና የተጣሩ ውህዶች ለሊድ አሲድ ባትሪ አምራቾች ግብአቶች ናቸው፡፡<br><br>የማጣሪያው ድስት በሁለት መልኩ ሊሞላ ይችላል፡፡ (1) የቀለጠ ብረት ከማቅለጫው በቀጥታ ወደ ማጣሪያ ድስቱ ይሞላል (ይህም ወደ 450 ዲግሪ ሴልሺየስ ይደርሳል) (2) የቀለጠውን ብረት ከማቃጠያው አውጥቶ ከ1-2 ቶን የሚደርስ ጉራጆችን በመስራትና በማቀዝቀዝ፤ እነዚህን የቀዘቀዙ የብረት ጉራጆች ወደ ማጣሪያ ድስቱ መሙላት ናቸው፡፡<br><br>ደህንነቱን የጠበቀና ውጤታማ ስራን ለመስራት ማጣሪያው ሊኖራቸው የሚገቡት መሰረታዊ ንድፎች የሚከተሉት ናቸው፡፡<br>• ማቃጠያዎችን በቀላሉ መጠገን ይቻል ዘንድ ድስቶቹ ከመሬት በላይ ከፍ ያሉ መሆን አለባቸው፡፡<br>• ማጣሪያው የሚሰራበት የወለለ አካባቢ ወደ ጣሪያው ከፍ ያለ ሆኖ አንድ ሜትር ከፍታ ላይ የእጅ መያዣ ኖሮት እንቅፋትን ከሚያስከትሉ መሰናክሎች ነፃ መሆን አለበት፡፡<br>• ወደ ጣሪያው ከፍ ያለው የስራ ወለል ለአደጋ መውጫ ያገለግል ዘንድ ሁለት መግቢያና መውጫዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡<br>• ሠራተኞችን ወደ ድስቱ ከመውደቅ ለመከላከል የድስቱ አፎች ቢያንስ ከወለሉ በአንድ ሜትር ከፍ ማለት አለባቸው፡፡<br>• የሊድ ጉራጆችን፣ ሌሎች ንጥረ ነገሮችን ወይም ውህዶችን ለመጨመር ካለሆነ በስተቀር በማንኛውም የሥራ ወቅት ድስቶቹ መዘጋት ይኖርባቸዋል፡፡<br>• ማቀላቀያዎችና የቀለጠ ብረት ወደ ድስቱ የሚጨምሩ ቱቦዎች ከድስቱ ከዳን ጋር አብረው ተጣብቀው መኖር ይገባቸዋል እንጅ መንቀል የለባቸውም፡፡<br>• ናሙናዎችን ለመውሰድና አንዳንድ ንጥረ ነገሮችን ለመጨመር ይረዳ ዘንደ በድስቱ ክዳን ላይ አነስተኛ በሮች እንዲኖሩት ይደረጋል፡፡<br>• ድስቶችና የብረት ማቅለጫዎቹ ከጭስና ብናኝ ማስወገጃ ጋር በቀጥታ መገናኘት |

| | | |
|---|---|---|
| | | አለባቸው::<br>• የቀለጠውን ብረት መቅዳትና ወደ ጠጣር ብርት የመቀየር ሂደት ከማጣሪያ ድስቱ የታችኛው ክፍል እንጂ በላይኛው ክፍል መደረግ የለባቸውም::<br><br>ከፍተኛ ሙቀት ያለውና የቀለጠ የሊድ ፍሰትን ያያዘ ስለሚሆን ሊድን የማጣራት ስራ፤ ብናኝን የመያዣ መንገዶችን ጨምሮ ጥብቅ የሆነ የጤናና የደህንነት እርምጃዎች ሊኖሩት ይገባል::<br><br>ሊድ ከብረት ጋር ሊቀላቀል ስለማይችል ከ10-200 ሜጋ ቶን መያዝ የሚችሉ ከብረት የተሰሩ ድስቶች ለማጣሪያው ሂደት ጥቅም ላይ ይውላሉ:: መጠናቸውም ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎች የመልሶ ዑደት ፋብሪካው ባለው የማስተላለፊያ መጠን ይወሰናል::<br><br>በማጣሪያው ሂደት ከቀለጠው ሊድ ጋር የተቀላቀሉት ቆሻሻዎች በማጣሪያው ላይ ግግር ቆሻሻን ይፈጥራሉ:: ግግሮቹ ደረቅ፣ አቧራማና ከባድ በመሆናቸው በሰው እጅ በቀላሉ ሊወገዱ አይችሉም:: ስለሆነም ከማሽን ጋር የተገጠመ አውቶማቲክ የግግር ማስወገጃን መጠቀም ፈጣንና ተመራጭ ዘዴ ነው:: ግግሩ በሰው እጅ እንዲወገድ የተፈለገ እንደሆነ፣ ለሠራተኞች የስራውን ክብደት ለመቀነስ ይረዳ ዘንድ ረጅም እጀታ ያለው ማንኪያ በመፈተሻው ከፍተት በማስገባት እጀታው ድጋፍ እንዲኖረው ያስፈልጋል:: ሠራተኞችም እንደ መተንፈሻ፣ ጠንካራ ኮፍያ፣ የፊት ጭንብል፣ ጓንት፣ ቱታና በት ጫማ የመሳሰሉ የግል ደህንነት መጠበቂያዎችን መልበስ አለባቸው::<br><br>ዝቃጮችን ለማጣራትና ቀሪውን ሊድ ጥቅም ላይ ለማዋል ይረዳ ዘንድ በማጣራት ሂደት ተለይተው የተያዙ ውህድ ዝቃጮች በማቅለጫ ውስጥ ገብተው በመልሶ ዑደት ውስጥ እንዲያልፉ ማድረግ ይቻላል:: ከሊድ ጋር የተቀላቀሉ ውህዶችን ልቀት ለመከላከል የውህድ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች የአየር ማጣሪያ ከተገጠመለት ማስተንፈሻ ጋር መገናኘት አለባቸው::<br><br>የሊድ ውህድን ለመፍጠር እንደ ካልሲየም፣ አንቲሞኒ፣ ብር እና አርሰኒክ ያሉ የተለያዩ ብረቶችን በመፈተሻ አናቱ በኩል ወደ ማቅለጫው መጨመር ይቻላል:: |
| 4.5 | የተረፈ ምርቶች አያያዝ | ከማቃጠያው የሚወጡ ዝቃጮች ሊድ ስለሚይዙ አደገኛ ቆሻሻዎች ናቸው:: ዝቃጮቹ በውሃ ሊሟሙ የችላሉ፤ ትኩስ በሆኑበት ሰዓት ደግሞ እሳትን ሊፈጥሩ ይችላሉ:: ከተሽከርካሪ ማቃጠያ የሚወጣ ዝቃጭ ያልተዋሀደ ካርቦን የያዘ ከሆነ በትኩስነቱ ያልታሰበ የእሳት አደጋን ይፈጥራል:: ስለዚህም የዝቃጭ ማጠራቀሚያው ከበድ ባለ የብረት ሰሌዳ መዘጋት አለበት፤ ቀስ ብሎ እንዲቀዘቅዝ በማድረግም የሊድ ቅንጣቶች ከማጠራቀሚያው ስር እንዲዘቅጡ ሲደረግ የሊድ ክምር ይሰሩና ይህም ተቀርፎ ወደ ማጣሪያ ድስት እንዲገባ ይደረጋል::<br><br>በማንኛውም ሁኔታ የጋለ ዝቃጭ የሊድ ነበልባልን ማስውጣት የሚችል ማስተንፈሻ በተገጠመለት የጭስ መውጫ በመታገዝ መቀዝቀዝ አለበት:: በተጨማሪም ከተሽከርካሪ ማቃጠያ የሚወጣ ዝቃጭ እርጥበትንና ካርቦን ዳይኦክሳይድን ከከባቢው አየር የመሳብ አቅም ስላለው ተሰባብሮ ብረትንና ሌሎችን መርዛማ ንጥረ ነገሮችን እንደ ዝቃጭ ወይም የላመ ዱቄት አድርጎ ያስቀራል::የተሰባበረው ዝቃጭ ለሰው ጤና መርዛማ ሊሆን ስለሚችል በእጅ ሊበጠርና ሊጣራ አይገባውም::<br><br>ይህን ያለፈ ዝቃጭ ከትትል ተደርጎበት መከኖና ጉዳት እንደማያደርስ ተረጋግጦ መያዝ ወይም ለቀጣይ ህክምና ፈቃድ ላለው የአደገኛ ቆሻሻ ማከሚያና ማስወገጃ መሰጠት አለበት:: ዝቃጮች ተጠራቅመው መቆየት ካለባቸው ለማከማቻነት የሚያገለግለው እርጥበትን የማያስተላልፍ ከኮንክሪት የተሰራ ማጠራቀሚያ፣ ክዳን ያለው፣የአየር ማስተንፈሻ የተገጠመለትና ከዝናብ፣ ከነፋስና ከጎርፍ ከለላ ያለው ቦታ መሆን አለበት:: ያልታከሙ ዝቃጮች ፈፅሞ ወደከባቢ መደፋት የለባቸውም:: በዝቃጭ ውስጥ የለው የሊድ ይዘት ክትትል በሚደረግበት ጊዜ የሊድ ይዘቱ ከ2% መብለጥ የለበትም:: ከ2% በላይ የሊድ ይዘት መገኘት ማቅለጫው ደረጃውን ያልጠበቀ እንደሆነና ማሻሻያ ሊደረግለት እንደሚገባ አመላካች ነው:: እንዲህ ዓነት ዝቃጮች ወደ ማቅለጫው ተመልሰው የሊድ ይዘታቸው እንዲቀንስ መደረግ አለበት:: ከ2% በታች የሊድ ይዘት ያላቸው ዝቃጮች (1) ፈቃድ ላለው የአደገኛ ቆሻሻ አስወጋጅ ተላልፈው በስርዓት ሊወገዱ ይችላሉ፤ ወይም (2) ከቤት ውጭ ላሉ ግንባታዎች ከሚውል ስሚንቶ ጋር ከ13-15% ተቀላቅሎ አገልግሎት እንዲሰጥ ሊደረግ ይችላል:: የሁለተኛውን መንገድ ለመጠቀም ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ኃላፊነት ባላቸው አካላት |

መርዛማ ቅንጣቶችን የማስረግ ሂደቱ ወይም የሰው ሰራሽ ፍሳሾች የማስረግ ሂደቱ ተመርምሮ ደረጃውን የጠበቀ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

የባትሪ ፍሳሽ (የባትሪ አሲድ) በተቀናጀ ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎች የመልሶ ዑደት ማከናወኛ ፋብሪካ ውስጥ በሚካሄድ የባትሪ ሰበራ ቁጥጥር ባለበት ሁኔታ ብቻ መወገድ አለበት (ክፍል 4.1ን ይመልከቱ)፡፡ የመሰብሰብና የማጓጓዝ ሂደትን ጨምሮ ባሉት የአያያዝ ሰንሰለቶች ሁሉ አላግባብ ፍሳሽ ሊኖር አይገባም፡፡ የአሲድ ፍሳሽ የውኃ ስነምህዳርን ሊጎዳ የሚችል የጨው ውህድ ሊኖረው ስለሚችል፤ ማንኛውም ፍሳሽ ቢመከንም እንኳን ወደ አካባቢ መደፋት የለበትም፡፡ የሊድ አሲድ ባትሪ ፈሳሽ ከውኃ ጋር የተቀላቀለ ሰልፈሪክ አሲድ (የፒ.ኤች መጠኑ ከ2 ያነሰ) ስለሆነ ከፍተኛ ዝገትን ያስከትላል፡፡ ስለሆነም ከአልኮል፣ ከአልካላይ፣ ከጠንካራ ቤዞች፣ ከሌሎች አሲዶች፣ ከብረቶች፣ ከተቀጣጣይ ነገሮችና ውህደት ሊፈጥሩ ከሚችሉ ንጥረ ነገሮች ርቆ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡ ማንኛውም ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎችን ለማከማቸት የተዘጋጀ ቦታ የፍሳሽ ማስወገጃ የተሰራለትና አሲድን መያዝ የሚችል ፍሳሽንም የማያሰርግ ወለል ሊኖረው ይገባል፡፡ ፈሳሽን በማያሰርግ መያዣ ውስጥ ተጓጉዘው ለተከማቹ የገለገሉ ባትሪዎች ግን ይህ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡

ከባትሪ አሲድ ጋር ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች ረጅም እጅጌ ያለው በጥጥ የተሰራ ልብስ፣ አሲድን የሚቋቋም ጓንት፣ ከፕላስቲክ የተሰራ ሽርጥ፣ የዓይን መከላከናያና ውኃ የማያስገባ የቦት ጫማ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ የባትሪ አሲድ መፈናጠሮች ሊኖሩ በሚችልባቸው አካባባቢዎች ሁሉ የዓይን መታጠቢያ ሊኖር ይገባል፡፡

ማንኛውም ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎችን ለማከማቸት የተዘጋጀ ቦታ የፍሳሽ ማስወገጃ ፈሰስ የተዘጋጀለትና አሲድን መያዝ የሚችል፣ ውሀ የማያሰርግ ወለል ሊኖረው ይገባል፡፡ ፍሳሽን በማያሰርግ መያዣ ውስጥ ተጓጉዘው ለተከማቹ ያገለገሉ የሊድ አሲድ ባትሪዎች ግን ይህ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡

የባትሪ ፍሳሽን በማስወገድ ጊዜ ሊኖሩ የሚገቡ ግንዛቤዎች፡-

- ባትሪው በመጋዝ የሚሰበር ከሆነ ከመሰበሩ በፊት አሲዱ ወደ ፍሳሽ ማከሚያ መገልበጥ አለበት
- መደሻ የተገጠመለት የባትሪ ወፍጮ ከፍሳሽ ማከሚያ ጋር ተገናኝቶ አሲዱን ወደዚያ ማስተላለፍ አለበት
